
መዛኙ
ሲመዘን
ቴዎድሮስ ደመላሽ



ማውጫ

መግቢያ.....5

ከታሪክ ጋር በተያያዘ

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነው?.....11

በሰብዓ ሰገል፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በበዓለ ጰራቅሊጦስ ቀን በነበሩት ኢትዮጵያውያን ጊዜ ነው....11

በጀንደረባው ጊዜ ነው.....12

በሐዋርያው ማቴዎስ ጊዜ ነው.....13

በፍሬምናጦስ ጊዜ ነው.....16

የከሣቴ ብርሃንን ታሪክ በተመለከተ.....17

ስሙን ማን አወጣለት?.....17

የየት አገር ሰው ነው?.....18

ከሀገሩ ይዞት የወጣው ማነው?.....19

አደጋ የጣሉባቸውን ሰዎች በተመለከተ.....20

ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ሁኔታ በተመለከተ.....22

ወደ ቤተ መንገሥት የገባው እንዴት ነው?.....23

ወደ ግብፅ የሄደው እንዴት ነው?.....25

ስልጣነ ክህነቱን በተመለከተ.....27



ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተያያዘ

ቀዳሚውን ቋንቋ በተመለከተ.....30
በመጀመሪያ ስለተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ.....32
ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት ወይስ የለባትም?.....34
የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ተብሎ
የሚታመነውን ሁኔታ በተመለከተ.....43
ሮሜ 8÷34 ላይ ያለውን ሐሳብ በተመለከተ.....45
የሰማንያ አሐዱ አቀባበልን በተመለከተ.....53
ማጠቃለያ.....67



© ቴዎድሮስ ደመላሽ
የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All right reserved

ነሐሴ 2012 ዓመተ ምሕረት

የአዘጋጁ አድራሻ

✉ 29783 ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
+251 94 66 57 513
E mail: tewoderosedemelash@gmail.com
Face book: www.facebook.com/tewodero.demelash

ምስጋና

ከእርሱ በሆነው ፍቅሩ ለወደደኝ፣ መጠን በሌለው ምሕረቱ ይቅርታውን ላበዛልኝ፣ ብቻውን ለነፍሴ መድኅን ላዘጋጀልኝ ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን፤ አሜን!

‹‹ውሃን የሚያናገረው ድንጋይ ነው›› እንደሚባለው ይህቺን አነስተኛ ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ምክንያት የሆነኝን ‹‹መዛኙ››ን በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡ እርሱ እንዲህ ያለ ‹‹የተዝረከረከ›› ሥራ አንብቡልኝ ብሎ ለአደባባይ ባያሰጣ በዚህች ጽሑፍ የቀረቡትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የተወናበዱ ትምህርቶችን ለማስነበብ አልታደልምና ውሃውን ያናገረውን ድንጋይ ማመስገኑ አግባብ ነው፡፡

ለዚህ ጽሑፍ ዝግጅት የረዱኝንና በዚህ ጽሑፍ ላይ ባልጠቀማቸውም በቀላሉ ላገኛቸው የማልችላቸውን መጻሕፍት እጄ እንዲገቡ የረዱኝን፤ አባይነሽ ቅባቱ፣ ቢንያም ገብረ ማርያም፣ ጴጥሮስ ጸጋዬ፣ ፍሬው አዱኛ፣



ወንድዬ ባርባ፣ ሄኖክ ጌቱ፣ ሙሉጌታ ያሬድና እንድሪስ ሐሰን ከልብ አመሰግናለሁ!!! ወገኖቼ ተባረኩልኝ!!!

ከዚህም በተጨማሪ ወዳጆቼ የሆኑት መሪጌታ ሙሴ መንበሩ፣ ምትኩ ፈቀደ፣ በድጋሚ አሁንም ስሙን የማነሣው ቢንያም ገብረ ማርያምና ሙሴ ክንደያ፣ እንዲሁም የፌሱ ቡኳ ጀግና ፀሐይ ታደሰ (ዲቦራ) እና አሳቢነታን፣ ፍቅሯንና አክብሮታን በብዙ መንገድ በመግለጽ ሁሌ የምታስገርመን ማስተዋል አስማረ እግዚአብሔር የሰጠኝ ቤተ ሰቦቼ ናችሁ!!! እናንተ ስጦታዎቼ ከአጠገቤ በመሆናችሁ ብርቱ ሆኛለሁ!!! ስለእናንተም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ!!! ወገኖቼ እግዚአብሔር አምላክ በነገር ሁሉ ይባርካችሁ!!! የልባችሁን መሻት ይፈጽምላችሁ!!!

መግቢያ

በተለያዩ ዘመናትና ምክንያቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡትን የስሕተት ትምህርቶች በቃለ እግዚአብሔር ተፈትሸው ለቅዱሱ ቃል ስፍራ ይልቀቁ የሚለውን የእንታደስ ጥሪ ለመቃወም በተለያዩ አካላት የተለያዩ መልእክቶች ቀርበዋል። ለዚህ ዓላማ ቢረዳ ተብሎ ከቀረቡት መጻሕፍት መካከል አንዱ ያረጋል አበጋዝ ከእኛ በቀር ሁሉም የተሳሳቱና የጠፉ ናቸው የሚለውን ሐሳብ ለማስተላለፍ ያዘጋጀው ‹‹መደሎተ ጽድቅ - ቅጽ 2››[1] የተሰኘው ነው።

[1] ይህቺ አነስተኛ ጽሑፍ በዝግጅት ላይ ሳለች ቅጽ ሦስት መድሎተ ጽድቅ ለንባብ በቅቷል። በቅጽ ሦስት ላይ፣ በተለይ ሮሜ 8÷34 ላይ የሚያስነብበው ነገር እንዳለ፣ በቅጽ ሁለት ላይ አጭር መልእክት በማስቀመጡ፣ የቅጽ ሦስትን መውጣት በጉጉት እጠብቅ ነበርና፣ መጽሐፉ እጄ እንደገባ፣ በቅድሚያ ያየሁት ‹‹ሮሜ 8÷34›› በሚል ርዕስ የተቀመጠውን ምዕራፍ ስምንትን ነበር። ከተለመደው አንጻር በተደጋጋሚ ይነሡ የነበሩት ኤርምያስ 7÷25፣ የ1934 ዓመተ ምሕረት ዕትምና ሌሎችም የሌሉ መሆናቸውን የሚመለከቱ ደጋፊዎቹ እነዚህን ሐሳቦች ከዚህ በኋላ አያነሡም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖር የ1934 ዓመተ ምሕረት ዕትምን በተመለከተ ‹‹ሮሜ 8÷34 እና የ1938 ዕትም ዐዲስ ኪዳን›› በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ አስነብባችኋለሁ።

ያረጋል በዚህ መጽሐፉ ላይ በርከት ያሉ ስሕተቶችን የሠራ ቢሆንም በዚህች አነስተኛ መልእክት ሁሉንም ማንሣት የማይቻል በመሆኑ አንዱን ነጥብ መሠረት በማድረግ ሰውየው በስሜት እንጂ በመረጃ የማይጽፍ መሆኑን ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። ለዚህም እንዲረዳ በቅድሚያ የያረጋልን ሐሳብ ቃል በቃል በማስፈር፣ ሐሳቡ የተገኘበት ምንጭ በአግባቡ ከተቀመጠ በኋላ፣ ሐሳቡ ምን ያህል የተሳሳተ እንደ ሆነ ለማሳየት፣ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ነጥቦች ቀርበዋል። መረጃ ሆነው የቀረቡትን መጻሕፍት በተመለከተ በተቻለ አቅም ከቤተ ክርስቲያንና ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ወይም ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ነን ከሚሉ ሰዎች እንዲሆን ጥረት ተደርጓል። ከዚህ ወጣ ካለ ግን ከታሪክ መጻሕፍት ላይ የተገኙ ሐሳቦችን ለማስፈር ተሞክሯል። ለዚህም ምክንያቱ የሚቀርበውን ሐሳብ ‹‹የቤተ ክርስቲያን አይደለም›› የሚል ምክንያት እንዳይነሣ ለማድረግ ነው።[2] የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ያረጋል

[2] አንዳንድ ለየት የሚሉ ሐሳቦች በአባቶችና በወንድሞች ሲነሡ ‹‹ይህማ የግለሰብ እንጂ የቤተ ክርስቲያን አቋም አይደለም›› የሚል ሐሳብ የሚሰጡ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች የሚዘነጉት ነገር 1) አሁን በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ የሚተቸው የያረጋል መጽሐፍ



በዳንሰ መረጃ ያቀረብኩት ነው ካለው ጽሑፍ ውስጥ፣ <u>አንዱን ነጥብ ብቻ ለይቶ በማውጣትና</u> የተለያዩ መረጃዎችን በማቅረብ ምን ያህል ከእውነታ የራቀ ጽሑፍ መሆኑን ማሳየት ነው።

የግለሰብ መጽሐፍ ቢሆንም ‹‹ኦርቶዶክስ መልስ አላት›› በሚል ማስተዋወቂያ ሲሰጡ የሚታዩት አነሱው ራሳቸው መሆናቸውን ነው፣ 2) አባቶችም ሆኑ ወንድሞች ቤተ ክርስቲያን መድረክ የሰጠቻቸው መሆኑን ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን በሚያስመሰግነው ድርጊታቸው ብቻ ሳይሆን በሚያስወቅሰው ሥራቸውም የቤተ ክርስቲያን ስም አብሮ መነሣቱ ተገቢ ነው። አለበለዚያ ግን ቤተ ክርስቲያን አላውቃቸውም አይወክሉኝም ካለቻቸው ወገኖች ይመደቡ!!!



መዘኙ ሲመዘን

የ‹‹መድሎተ ጽድቅ - ቅጽ 2›› መጽሐፍ አዘጋጅ መልስ እሰጣለሁ በሚል የገባበት አጣብቂኝ አላስወጣው ብሎ በብዙ ሲጨነቅ ይታያል። በዚህ ጭንቀቱ ካሰፈራቸው መያዣ መጨበጫ ከሌላቸው ጽሑፎች ውስጥ ‹‹... በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር አይችልም...›› በሚል ያሰፈረው አንዱ ነው። ሙሉው ሐሳቡ እንደሚከተለው ይነበባል፤

> ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የቅዱስ ትውፊት ምልዐታዊ አካል አድርጋ ስለምትረዳውና ስለምትይዘው ይህ አረዳዷ ‹መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ› ከሚሉት ፕሮቴስታንቶች ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን በእውነትና በተጻፈበት ዓላማ ለመጠበቅ የምትችለው እርሷ ናት። ምክንያቱም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር አይችልም፤ መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት

አላትና፡፡ በአንጻሩ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ ግን እንኳንስ ቅዱሱ የእግዚአበሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስተምረውና ሊደግፈው ቀርቶ በጽኑ የሚቃወመው ነገር ሁሉ በስሙ እየተነገረና እየተደረገ ነው፡፡ ፕሮቴስታንቲዝም በባሕርዩ ይህን መቃወምና መከላከል አይችልም፤ ምክንያቱም ደጋግመን ለማየት እንደሞከርነው አንደኛው ‹እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው› ብሎ ቢነሣ፣ ሌላኛው ‹‹ትክክል አይደለህም› ብሎ ለመቃወም አቅም አይኖረውም፤ ከመጀመሪያው ግላዊ አረዳድ የተፈቀደ ነውና፡፡[3]

ከዚህ ከያረጋል ጽሑፍ የምናገኘው ሐሳብ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፤

- ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር አይችልም፣
- ምክንያቱም መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት አላት፣

[3] ያረጋል አበጋዝ (ዲያቆን)፣ መድሎተ ጽድቅ - ቅጽ 2 (ታኅሣሥ 2012) ገጽ 177፡፡

በዚህ መቆጣጠሪያና መለኪያ መሰረት ‹እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው› ብሎ አንዱ ቢነሣ፣ ሌላኛው ‹‹ትክክል አይደለህም› ብሎ በመቃወም ከግላዊ አረዳዱ መልሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያመጣዋል፣

- ግላዊ አረዳድ የተፈቀደ አይደለም፤

የሚለውን ነው፡፡ ይህን ሐሳብ ለማሳየት ግን ምንም ያቀረበው መረጃ ያለመኖሩ ትምህርቱ መሠረት የሌለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ ከላይ የቀረቡትን ነጥቦች የሚያፈርሱ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሙላት መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆኑ ነጥቦች በሁለት መንገዶች ማለትም በታሪክና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አላቸው ተብለው በሚታመኑ ሐሳቦች ላይ ቀርበዋል፡፡ ይህንም ከዚህ በታች በነጥብ በነጥብ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡-

ከታሪክ ጋር በተያያዘ

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነው?

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነው? የሚለውን በተመለከተ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እርስ በእርስ የሚግባቡ አይመስልም። ይህም የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግላዊ አረዳድ ከልካይ የሌለው መሆኑን ነው። ይህንም በነጥብ በነጥብ በማስቀመጥ ላሳያችሁ፡-[4]

1. በሰብዓ ሰገል፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በበዓለ ጰራቅሊጦስ ቀን በነበሩት ኢትዮጵያውያን ጊዜ ነው

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው ኢየሱስ አገልግሎት ሳይጀምር፣ ሐዋርያት ሳይመረጡና ለወንጌል አገልግሎት ሳይሰማሩ ነው፣ የሚሉ ወገኖች የሚከተለውን ያስነበባሉ፤ ‹‹ለኢትዮጵያ <u>ክርስትና ሃይማኖትን ያስገቡት ቀደም ሲል</u>

[4] ከዚህ በታች የቀረቡት መረጃዎች ላይ አንድን ሐሳብ መሠረት አድርገው የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍት የተለያዩ ግላዊ አመለካከቶች እያቀረቡ እንዳሉ ለማስተዋል ይረዳዎ ዘንድ ጎላ ያለ መስመር የተደረገባቸውን ቦታዎች ይመልከቱ!!!

ሰብዓ ሰገል፣ ጌሳም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ውሎ አድሮም በበዓለ ጰራቅሊጦስ ቀን የነበሩት ኢትዮጵያውያን [ናቸው]...››።[5] በዚህ ሐሳብ መሠረት ጀንደረባው ከቍጥር ጎድሎ ይታያል። ይህ እንግዲህ አንዱ ግላዊ አረዳድ መሆኑ ነው፤ ሌላው ደግሞ በቀጣዩ ይታያል።

2. በጀንደረባው ጊዜ ነው

‹‹ሀንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር›› ተብሎ በወንጌላዊው ሉቃስ የተዘገበለት ጀንደረባ ለመስገድ ከሄደበት ከኢየሩሳሌም ሰግዶ ብቻ ሳይሆን የምሥራች የሆነውን ቅዱሱን ወንጌል ሰምቶና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ‹‹ደስ ብሎት›› ጉዞውን ቀጠለ።

ጀንደረባው ከፊልጶስ ወንጌልን ከሰማ በኋላ ወደ ወገኖቹ መጥቶ የሰማውን በማሰማት ከቤተ መንግሥት ጀምሮ ያሉ ሰዎች ሁሉ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ አድርጓል የሚል

[5] አማረ አፈለ ብሻው፣ ኢትዮጵያ የሰው ዘር የተገኘባት የእምነትና የሥልጣኔ ምንጭ ናት፤ (ጥር 2004) ገጽ 147 - አጽንዖት የግል። ማኅበረ ቅዱሳን፣ ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ - አንደኛ መጽሐፍ (1988) ገጽ 94።

ሐሳብ ይቀርባል፡፡ ከዚህም በመነሣት ‹‹<u>የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በንግሥት ህንደኬ ዘመነ መንግሥት በጀንደረባዋ ባኮስ አማካይነት በ34 ዓመተ ምሕረት ሲሆን</u> የክርስትና ሃይማኖትን የተቀበለች ብቸኛ እና ቀደምት የአፍሪካ ሀገር ኢትዮጵያ…›› ናት ይላሉ፡፡[6]

3. በሐዋርያው ማቴዎስ ጊዜ ነው

ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ‹‹በትግራይ በስተምዕራብ በአድዋ አውራጃ ልዩ ስሙ ናዕጼር በተባለ ቦታ›› ወንጌልን ሰብኳል በሚል የሚጠቀሰው ሌላው ደግሞ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ነው፡፡[7]

> ሩፊኖስና ሶቅራጥስ የተባሉ ታሪክ ጸሐፊዎች ሐዋርያት በዓለም ለማስተማር ዕጣ በተጣጣሉበት ወቅት ፋርስ ለማትያስ ኢትዮጵያ ደግሞ ለማቴዎስ ደረሰች ብለው በጻፉት መሠረት ማቴዎስ ኢትዮጵያ ውስጥ

[6] ካሳሁን ደምሴ ወርቁ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐበይት ፈተናዎች፤ (መጋቢት 2007) ገጽ 36-37 - አጽንዖት የግል፡፡

[7] ማኅበረ ቅዱሳን፣ ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ - አንደኛ መጽሐፍ፤ (1988) ገጽ 95፡፡

ሲያስተምር በሰማዕትነት ዐረፈ ይላሉ፡፡ በሰሜን ኢጣልያ ፒስ በተባለው ቦታ በሚገኘው በቅዱስ ማቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማቴዎስ የሞተውን የኢትዮጵያ ንጉሥ ልጅ በተአምር በማስነሣቱ የተደነቀው አረማዊው ንጉሥና ዜጎቹ ክርስትናን እንደተቀበሉ የሚገልጹ ሥዕሎች አሉ፡፡ ሆኖም በቤተ ክርስቲያናችን የማቴዎስ ኢትዮጵያ ውስጥ ማስተማርና በሰማዕትነት ማረፍ የሚገልጽ የጎላ ታሪክ አይገኝም፡፡[8]

ይህ፤ ወንጌል በዘመነ ሐዋርያት በቅዱስ ማቴዎስ እጅ ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚለው አንዱ ‹‹ግላዊ አረዳድ›› ሲሆን ይህን ሐሳብ አፈር ከድሜ የሚያስበላው ሌላው ‹‹ግላዊ አረዳድ›› ደግሞ እንዲህ ይላል፤

ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ስፍራ የምትሰጣቸውና በርከት ባሉ የሥነ ጽሑፍ ሥራቸው የሚታወቁት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ‹‹ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን እንዲህ አይደለም፤

[8] ሉሌ መልአኩ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ (1997) ገጽ 22፡፡ ጎርጎርዮስ (አባ)፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ህዳር 1986 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 20፡፡

የሐዋርያት እግር በርሷ ላይ አልተመላለሰም፡፡ የጌታም ተአምራት በውስጧ አልተደረገም፡፡ በዜና አመነችው በድምፅም ተቀበለችው እንጂ››[9] በማለት ወንጌላዊው ማቴዎስ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ሠርቶታል የሚባለውን የወንጌላዊነት ሥራ ገደል ይከቱታል፡፡ መምህር ደሴ ቀለብም ከአቡነ ሰላማ ጀምሮ የተሾሙትን ጳጳሳት ‹‹የግእዙ መረጃ እንዲህ ይዘረዝረዋል›› ባሉበት ምንባብ ‹‹… አትናቴዎስ ፍሬምናጦስ የሚባለውን ከሣቴ ብርሃን ሰላማን ሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ሰደደው፡፡ [ፍሬምናጦስም] አስተምሮ አሳምኖ የኢትዮጵያን ሰዎች አጠመቃቸው፡፡ ክርስትና በከሣቴ ብርሃን ሰላማ ጊዜ በኢትዮጵያ ተጀመረ፡፡ ከሰላማ አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ ፩ ሐዋርያ አልመጣም ነበርና፡፡ ከ፲፪ ሐዋርያት እጣም በተጣጣሉ ጊዜ ሐዋርያት አገሩን ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ የለም ነበር›› የሚለውን ጠቅሰው አስነብበዋል፡፡[10] ይህም (ማቴዎስ መጥቶ ሰብኳል የለም አልሰበከም የሚለው) ግላዊ አረዳድ ያመጣው አለመግባባት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

---

[9] ጊዮርጊስ (አባ)፣ መጽሐፈ ምሥጢር፤ ሕሩይ ኤርምያስ (መምህር) (ተርጓሚ) (መጋቢት 2001) ገጽ 56፡ 59፡ 60 - አጽንዖት የግል፡፡

[10] ደሴ ቀለብ (መምህር)፣ ታሪክ ነገሥት ከምኒልክ ፩ኛ እስከ ምኒልክ ፪ኛ (2007) ገጽ 143 - አጽንዖት የግል፡፡

4. በፍሬምናጦስ ጊዜ ነው

ፍሬምናጦስ (ከሣቴ ብርሃን፣ አባ ሰላማ) ወንጌልን ለኢትዮጵያውያን ማስተማሩንና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለ ውለታ መሆኑ በታሪክ ጸሐፊዎችም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት አለው።

እነርሱም፤ ‹‹<u>ኢትዮጵያ ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል በይፋ የተሸጋገረችው በ334 ዓመተ ምሕረት ነበር</u>።... የክርስትና ሃይማኖትን አምኖ በመቀበል የአገሪቱ ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑን በይፋ ያወጀው አጼ አብርሃ ነበር። የመጀመሪያው የአክሱም ጳጳስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (አቡነ ፍሬምናጦስ) ከአጼ አብርሃም ጋር በመተባበር የክርስትና ሃይማኖትን አስፋፋ›› ይላሉ።[11]

ቀደም ሲል እንደቀረበው ከሆነ፣ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው መቼ ነው? የሚለውን በተመለከተ ‹‹አለ›› የተባለው ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› በወሬ እንጂ በተግባር የሌለ በመሆኑ፣ ‹እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው› በሚል መንፈስ ‹‹ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን

[11] ሳሙኤል አለማየሁ ታዬ፣ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር (መስከረም 27 ቀን 2005) ገጽ 21-22 - አጽንዖት የግል።

ግምትና ስሜት...›› ጽፎ አንብበናል፡፡ በዚህም ‹‹ግላዊ አረዳድ የተፈቀደ አይደለም›› እንባል እንጂ ከልካይ የሌለ መሆኑን ለመታዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ በታችም ይህንኑ ሐሳብ የሚያጠናክሩ ነገሮችን እናገኛለን፡፡

የከሣቴ ብርሃንን ታሪክ በተመለከተ

1. ስሙን ማን አወጣለት?

ሰላማ የሚለውን የፍሬምናጦስን ስም በተመለከተ በአንድ መጽሐፍ ላይ ብቻ የሐሳብ መለዋወጥ እናያለን፡፡ በዚህም ደግሞ በልዩ ልዩ ጸሓፍት ብቻ ሳይሆን በአንዱ መጽሐፍ ላይ ብቻ አለመግባባቶች መኖራቸውን ለመረዳት እንችላለን፡፡

ከራሱ መግባባት ያቀተው መጽሐፍ በአንድ በኩል ‹‹... ሊቀ ጳጳሱ አባ ጢሞቴዎስም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቆ ቅብዐ ሜሮንን ቀቡቶ ስሙን ሰላማ አለው፡፡ እሱም በምስጋናውና በአማረ ቃሉ የቤተ ክርስቲያን ሰላሚ ነውና ...›› በሚል ‹‹ሰላማ›› የሚለው ስም የተሰጠው በጥምቀት ስርዓት ወቅት ነው ይለንና፤ መልሶ ደግሞ አቡነ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ‹‹... በመስቀል ምልክት አማትቦ ባረከው፤ በዚህን ጊዜ ይህ ሊቀ

ጳጳሳት ስለ ብፁዕና ስለ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ስለ ደጋጮች አብርሃና አጽብሓ ስለ ኢትዮጵያ ሰዎች አምልኮታቸውና ክርስቶስን ስለ መውደዳቸው ስለ ጸና ሃይማኖታቸውም ፈገግ ብሎ እጅግ ተደሰተ ሊቀ ጳጳሳትም መልሶ ከዛሬ ጀምሮ ስምህ ፍሬምናጦስ አይሁን ብሎ ስሙን ለውጦ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አለው። ከሣቴ ብርሃንም ማለት ሃይማኖትን ገልጦ የሚያስተምር ማለት ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ በዚህ ስም ተጠርተሃልና አለው። ሰላማም ማለት እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስታርቅ ማለት ነው›› በማለት ስሙ የተሰጠው በጥምቀት ጊዜ ሳይሆን ስልጣነ ክህነቱን ሲቀበል ነው የሚል ሐሳብ ያቀርባል።[12]

2. የየት አገር ሰው ነው?

ፍሬምናጦስ ጢሮሳዊ ነው የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ።[13] የሶርያ ተዋላጅ መሆኑን ያሰፈሩ ሰዎችም አሉ።[14] እንደገናም ደግሞ የትውልድ አገሩን ወደ ኢየሩሳሌም

[12] አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998) ገጽ 3፡ 10።

[13] ብርሃኑ ድንቄ፣ የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ (1941) ገጽ 13።

[14] እርቅይሁን በላይነህ፣ አምስቱ የመከራ ዘመናት ቅጽ 1 (ጥር 2007) ገጽ 14

የሚወስዱትም ሰዎች አሉ።[15] ከዚህ በተለየ ሁኔታ ‹‹አገሩ ግሪክ መኖሪያው በጢሮስ…›› ነው በማለት ሁለቱን ለማስታረቅ የሞከሩም አይጠፉም።[16] ይህን ሁሉ ምን አመጣው? ከተባለ ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› በወሬ እንጂ በተግባር የሌለ በመሆኑ፣ ‹እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው› በሚል መንፈስ ‹‹ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት…›› በመጻፉ መሆኑ ግልጽ ነው።

3. ከሀገሩ ይዞት የወጣው ማነው?

ፍሬምናጦስን ይዞት ወደ ኢትዮጵያ ወደብ የመጣውን ሰው ማንነነት በተመለከተ አንዳንዶች ‹‹ዘመድ› ነው በሚል ሲያስቀምጡት።[17] ሌሎች ደግሞ ‹‹አባት› ነው በሚል

---

[15] አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998) መቅድም ቁጥር 1 እና ገጽ 2።

[16] ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ዋዜማ (2001 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 110።

[17] ኅርኅርዮስ (አባ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ህዳር 1986 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 21። ሉሌ መልአኩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ (1997) ገጽ 22። መርሻ አለኸኝ (ዲያቆን)፣ ዜና ጳጳሳት ኢትዮጵያውያን፤ (1996) ገጽ 14። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ (ሐምሌ 1988) ገጽ 109። ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀ/ዶ/ር)፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ) - አንደኛ መጽሐፍ፤ (2000) ገጽ 155።

ያስነብባሉ።።[18] ይህም ወጥነት የሌለውን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ያሳያል።

4. አደጋ የጣሉባቸውን ሰዎች በተመለከተ

አደጋ ያደረሱባቸውን ሰዎች በተመለከተ ልዩ ልዩ አመለካከት ያለ ይመስላል። ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ ‹‹... በጉዞአቸው ጊዜ በአፍሪካ የባሕር ጠረፍ በቀይ ባሕር ወደብ ውሀ ለመጠጣት አገር ለማየት ከጀልባቸው ወርደው ጀልባቸውንም ከወደብ አስጠግተው ሳሉ <u>በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች</u> በጀልባዎቱና በተሳፋሪዎቹ ላይ አደጋ ጥለው ዕቃቸውን ዘረፏቸው። ሜሮጵዮስንና የጀልባዎቱን ቀዛፊዎች እዚያው ገደሏቸው። እንደ አጋጠሚ ሆኖ ሁለቱ ወጣቶች ብቻ ከመገደል አምልጠው በአንድ ዛፍ ሥር ተጠግተው ሲጸልዩና መጽሐፍ ሲያነቡ ተገኙ፤ ያገኟቸውም ሰዎች በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሳያደርሱ በፈረስ አንገት፣ በጦር አንደበት የተማረኩ ሰዎች አመጣንልህ ብለው ለንጉሣቸው ሰጡት›› ሲሉ፤[19] ሌሎች ደግሞ ‹‹በሮማና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል ጠብ ተፈጥሮ ስለ ነበር

[18] ጋስፓሪኒ ገ.ማ. (አባ)፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ (የታተመበት ዘመን ያልተጠቀሰ) ገጽ 123

[19] ጎርጎርዮስ (አባ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ህዳር 1986 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 22።

ወደብ ጠባቂዎች ክሮማ ግዛት የመጡ መሆናቸውን በመገንዘብ ሜሮጲዮስንና በመርከቢቱ ውስጥ የነበሩ ሰዎችን ገድለው ሁለቱን ሕፃናት ለአካባቢው ገዥ ለባሕር ነጋሽ አስረከቡ›› ይላሉ::[20]

ከዚህ የተለየ ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ደግሞ ‹‹በቀይ ባሕር ላይ በመርከብ ሲጓዙ ምግብና ውሀ ስላለቀባቸው ለጉዞአቸው የሚሆን ምግብና ውሀ ለመፈለግ (አገር ለመጎብኘት[ም] ይባላል) የኢትዮጵያ ንግድ ማእከል በነበረችው የባሕር ጠረፍ አዱሊስ አጠገብ አረፉ:: ኢትዮጵያ ያን ጊዜም የቅኝ ግዛትን ትከላከል ኖሮ፣ የሮማውያንን የቅኝ ግዛት መስፋፋት በመቃወም በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሰዎችም በመልክ ሮማውያንን በመምሰላቸው ትላልቆቹን ሜሮጵዩስንና የመርከቡን ቀዛፊዎች በሙሉ ይዘው እዚያው ገደሉአቸው:: ወጣቶቹን ፍሬምናጦስንና ኤዲስዮስን ግን ለአካባቢው ገዢ ለባሕረ ነጋሽ[21] ወስደው አስረከቡ›› የሚል ያስነብባሉ::[22] ሜርጵዩስ

---

[20] ሉሌ መልአኩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ (1997) ገጽ 23:: እርቅይሁን በላይነህ፣ አምስቱ የመከራ ዘመናት ቅጽ 1 (ጥር 2007) ገጽ 14::

[21] ቀደም ሲል በቀረበው መረጃ ላይ አቡነ ጎርጎርዮስ ‹‹... በፈረስ አንገት፣ በጦር አንደበት የተማረኩ ሰዎች አመጣንልህ ብለው



ዘመዶቹን ፍሬምናጦስ እና ኤዺስዮስን ይዞ በመርከብ በሚጓዙበት ጊዜ ሽፍቶች (ወንበዴዎች) ጥቃት ያደረሱባቸው መሆኑን የጠቀሱም አሉ።[23]

5. ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ሁኔታ በተመለከተ ግሪካዊ የሆነው ሜርጵዩስ ልጆቹን ፍሬምናጦስ እና ኤዺስዮስን ይዞ በመርከብ በሚጓዙበት ጊዜ ሽፍቶች ጥቃት ያደረሱባቸው በመሆኑ አባታቸው ሲሞት ወንድማማቾቹን በጊዜው ወደ ነበረው ንጉሥ ዘንድ ወሰዷቸው የሚለውን ታሪክ የሚቀበሉ ሰዎች አሉ።[24]

ገድለ ከሣቴ ብርሃን ግን የተለየ ሐሳብ አለው፤ ሐሳቡን ‹‹... ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ በሁለት መቶ

ለንጉሣቸው ሰጡት›› ማለታቸው ይታወሳል። እዚህ ስፍራ ላይ የተጠቀሱት ጸሐፊ ደግሞ፤ ‹‹...ለአካባቢው ገዢ ለባሕረ ነጋሽ ወስደው አስረከቡ›› በማለት ርክክቡን ከንጉሡ ወደ የአካባቢ ገዢ ያወርዱታል። ይህም የግል አረዳድ አንዱ መገለጫ ነው።

[22] ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀ/ዶ/ር)፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ) - አንደኛ መጽሐፍ፤ (2000) ገጽ 156-157።

[23] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ (ሐምሌ 1988) ገጽ 109። ስንክሳር ገጽ 625።

[24] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ (ሐምሌ 1988) ገጽ 109።

ሃምሳ ሰባት ዓመተ ምሕረት ዓሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ ከዚህ በኋላ ብፁዕና ቅዱስ መስተጋድል ፍሬምናጦስ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ አገር ስሙ ሜርጵዮስ ከሚባል ከአንድ ነጋዴ ጋር መጣ። ከእነሱም ጋር አድስዮስ የሚባል አንድ ልጅ ነበር <u>የእግዚአብሔር መልአክ እየመራቸው በደህናና በሰላም ነጻነት ወደ አለበት አገር ደረሱና እጅግ ተደሰቱ</u>። ሰላማም ደስ የሚያሰኙና የሚያስደንቁ ነገሮችን አየ ሰባት ወርም በዚያ ተቀመጡ። ሜርጵዮስም ወደ አገሩ ይመለስ ዘንድ ተነሥቶ ሲሄድ በበረሃ የሚኖሩ ሽፍቶች በእሱ ላይ ተነሥተው ከእሱ ጋር ከአሉት መንገደኞች ጋር ገደሉት እነዚህም ልጆች በእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ተረፉ የዚያ አገር ሰዎችም እነዚያን ሕጻናት ማርከው ወስደው ስሙ አልአሜዳ ለሚባል ለአክሱም ንጉሥ ሰጡት›› በማለት አስነብቧል።[25]

6. ወደ ቤተ መንገሥት የገባው እንዴት ነው?

ቀደም ሲል እንደቀረበው ግሪካዊ የሆነው ሜርጵዩስ ልጆቹን ፍሬምናጦስ እና ኤዴስዮስን ይዞ በመርከብ በሚጓዙበት ጊዜ ሽፍቶች ጥቃት ያደረሱባቸው በመሆኑ

[25] አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998) ገጽ 4-5።

አባታቸው ሲሞት ወንድማማቾቹን በጊዜው ወደ ነበረው ንጉሥ ዘንድ ወሰዷቸው የሚለውን ታሪክ የሚቀበሉ ሰዎች አሉ።[26] በዚህም ወደ ቤተ መንግሥት ለምንና እንዴት ሄዱ የሚለው በግልጽ ይታያል።

ፍሬምናጦስ ወደ ቤተ መንግሥት ከዚህ በተለየ መንገድ የገባ የሚያስመስል ጽሑፍ በሚከተለው መልኩ ይነበባል፤ ‹‹ወጣቶቹ ነገሥታት ኢዛና እና ሳይዛና እንደ ልማዳቸው ከሊቀ ካህናቱ ጋር ስለ እግዚአብሔር ገናናነት ሲነጋገሩ እኛስ ስለ አንድ ነገር እንጨነቃለን አሉት፤ ሊቀ ካህናቱም ‹ጌቶቼ ሆይ የሚያስጨንቃችሁ ምንድን ነው? መንግሥታችሁንስ የሚያውክ ማን ነው?› ብሎ ጠየቃቸው። እነሱ ግን ‹አኮ በእንተ መንግሥተነ አላ በእንተ ልደተ እግዚእነ ክርስቶስ ውእቱ› ማለትም ‹ስለ መንግሥታችንስ አይደለም፤ ስለ ጌታችን ስለ ክርስቶስ መወለድ ነው እንጂ› አሉት። እሱም ‹ጌቶቼ ይህስ ምሥጢር ለእኔም ድንቅ ነው፤ <u>ነገር ግን በአልዓሜዳ ዘመን የመጣ ፍሬምናጦስ የሚባል አንድ ሰው አለ፣ እሱም እናንተ የኢትዮጵያ ሰዎች ግዝረትና እምነት</u>

[26] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ (ሐምሌ 1988) ገጽ 109።

አላችሁ ጥምቀትና ቁርባን የላችሁም እያለ ይናገራል አላቸው። ነገሥቱም ፍሬምናጦስን አስጠርተው ስለ ነገረ ትስብእቱ ምሥጢር እንዲያስረዳቸው ጠየቁት...›› በማለት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በቀጥታ ወደ ቤተ መንግሥት የሄደ ሳይሆን ከጊዜ በኋላ ሊያውም በሊቀ ካህናቱ ምስክርነት በነገሥታቱ በተደረገለት ግብዣ ነው ይላሉ።[27] መልሰው ደግሞ ‹‹ፍሬምናጦስ እነዚህን ልጆች (ኢዛና እና ሳይዛናንን) አካለ መጠን እስኪደርሱ ድረስ በክርስቶስ ማመን ሲያስተምራቸው ቆይቷል›› በማለት ቀደም ሲል ካሰፈሩት ሐሳብ የተለየ ነገር ሲያስነብቡም ይታያል።[28]

7. ወደ ግብፅ የሄደው እንዴት ነው?

‹‹ንጉሡ በሕይወት በቆየበት ጊዜ በንጉሥ ቤት ተቀመጡ። ለሞት በተቃረበበት ጊዜ አርነት አወጣው። ወደ ወደዱትም እንዲሄዱ አሰናበታቸው። ሲድራክስ ወደ ሀገሩ ወደ ጢሮስ ተመለሰ ፍሬምናጦስም ለኢትዮጵያ ሰዎች ለመዳናቸው

[27] ኃይለ ሥላሴ አለማየሁ (መምህር)፣ ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ (1989) ገጽ 5። ዐሥራት ደስታ (መምህር)፣ ከፍያለው ጥላሁን (ዲያቆን) እና አሳምነው ካሣ፣ ነገረ ቅዱሳን - ፪ (1998) ገጽ 24 - አጽንዖት የግል።

[28] ዐሥራት ደስታ (መምህር)፣ ከፍያለው ጥላሁን (ዲያቆን) እና አሳምነው ካሣ፣ ነገረ ቅዱሳን - ፪ (1998) ገጽ 30።



ምክንያት ይፈልግ ዘንድ ወደ እስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ሄደ›› በሚል የሰፈረውን ለተመለከተ አንባቢ ደግሞ ፍሬምናጦስ ወደ ግብፅ የሄደው ማንም ሳይጠይቀው በራሱ ተነሣሽነት እንደ ሆነ ነው የሚረዳው::[29]

ከዚህ በተለየ መንገድ የቀረበው ትረካ ደግሞ የሚከተለውን ያስነብባል፤ ‹‹የሥርዓተ ክህነትና ቁርባን መምጣት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለንጉሡና ለቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች አጽንቶ ነገራቸው::... በቤተ መንግሥቱና በሕዝቡ ተልኮ ወደ እስክንድርያ ሄደ›››::[30]

ሌላው ወደ ግብፅ ከሄደ በኋላ ያጋጠመው ነገር በተመለከተ ሁለት ዓይነት ነገር ቀርቦ አንብብናል፤

---

[29] (ጊዮርጊስ (አባ)፣ መጽሐፈ ምሥጢር፤ ሕሩይ ኤርምያስ (መምህር) (ተርጓሚ) (መጋቢት 2001) ገጽ 59:: ስንክሳር ገጽ 625:: ብርሃኑ አበጋዝ (መምህር)፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከዓለም እስከ ኢትዮጵያ (2009) ገጽ 222::

[30] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ (ሐምሌ 1988) ገጽ 110:: ካሳሁን ደምሴ ወርቁ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐበይት ፈተናዎች፤ (መጋቢት 2007) ገጽ 46:: ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 69:: እርቅይሁን በላይነህ፣ አምስቱ የመከራ ዘመናት - ቅጽ 1 (ጥር 2007) ገጽ 16::



- ፍሬምናጦስ ወደ ግብፅ በሄደበት ጊዜ በአርዮስ ምክንያት በነበረው ሃይማኖታዊ ውይይት የተነሣ በጊዜው ማንንም ማግኘት ባለመቻሉ <u>ለአንድ ዓመት በግብፅ ለመቀመጥ ተገዶ ነበር</u>።[31]

- ገድለ አቡነ ሰላማ ቀደም ሲል ከቀረበው በተለየ መንገድ ‹‹የተመረጠ ከሣቴ ብርሃን አባታችን አቡነ ሰላማ ከእዚያ ደረሰ። የእስክንደርያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ አትናቴዎስ የቅዱሰ ፍሬምናጦስ <u>መምጣቱን አውቆ</u> ከዙፋኑ ተነሥቶ ብፁዕና ቅዱስ ፍሬምናጦስ ወደ አለበት ሄዶ <u>በጎዳና ተቀበለው</u>›› የሚል ንባብ ያቀርባል።[32]

8. ስልጣነ ክህነቱን በተመለከተ

ፍሬምናጦስ ስልጣነ ክህነት ያገኘበት ሁኔታን በተመለከተ ያለውም ነገር እዚህና እዚያ የሚረግጥ አንድ መልክ

[31] ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀ/ዶ/ር)፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ (ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ) - አንደኛ መጽሐፍ፤ (2000) ገጽ 159።

[32] አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998) ገጽ 9 - አጽንዖት የግል።

የሌለው መሆኑን በሚከተሉት ነጥቦች መመልከት ይቻላል፡፡

አትናቴዎስ ከዲቁና ተነሥቶ ቀስ በቀስ እስከ ጵጵስና የደረሰ አባት ሆኖ ሳለ ‹‹... በአንድ ጊዜ ለቅዱስ አባ ሰላማ ጵጵስናን ሰጠ ማለት ያስቸግራል›› የሚሉት ካሣሁን ደምሴ፤ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ሕጻን ነው በማለት ክርስትናን ራሱ የተማረው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነና ከአትናቴዎስ ጵጵስንና ለመቀበል የሚያበቃውን ክህነት ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ውስጥ አግኝቶ እንደ ነበር ጠቁመዋል፡፡[33]

ሌሎች ደግሞ ፍሬምናጦስ በቀጥታ ጵጵስናን የተሾመ ወይም ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ሳለ ስልጣነ ክህነት የነበረው ሆኖ አትናቴዎስ ጵጵስናን የሰጠው ሳይሆን ‹‹... ቅስና ሾመው ቀጥሎም... ጵጵስና ሾመው...›› በማለት ቀደም ሲል ከቀረበው ሐሳብ የተለየ ሐሳብ ያስተላልፋሉ፡፡[34]

---

[33] ካሳሁን ደምሴ ወርቁ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐበይት ፈተናዎች፤ (መጋቢት 2007) ገጽ 40፡ 43 - የግርጌ ማስታወሻ እና ገጽ 45፡፡

[34] ኃይለ ሥላሴ አለማየሁ (መምህር)፣ ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ (1989) ገጽ 6፡፡

ገድለ አቡነ ሰላማም በበኩሉ ‹‹... እመቤታችን ማርያም ተገልጣለት ዲቁናና ቅስናን መቀበል ይገባሃል፤ ለጽጽሰና ተዘጋጅ እግዚአብሔር ይህቺን ከፍ ያለችውን ማዕረግ ሰጥቶአልና...›› አለችው የሚለውን ያስነብባል።[35]

ቀደም ሲል ከታሪክ ጋር በተያያዘ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ራሷ ቤተ ክርስቲያን ለንባብ ያበቃቻቸው መጻሕፍት ግላዊ አረዳዳቸውን ለንባብ ማብቃታቸውን ለማሳየት ተሞክሯል። በያረጋል መጽሐፍኮ መጽሐፍ ቅዱስን እንጂ ታሪክን በተመለከተ የሰፈረ ነገር የለም የሚል አንባቢ ቢኖር፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተያያዘም ቢሆን ግላዊ አረዳድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ምን እንዳለ ለመመልከት ከዚህ በታች የሰፈሩትን ነጥቦች በአግባቡ እንዲያነባቸው ይጠየቃል።

[35] አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998) ገጽ 7።



ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተያያዘ

ቀዳሚውን ቋንቋ በተመለከተ

የመጀመሪያው ቋንቋ ምንድን ነው? የሚለውን በተመለከተም እንዲሁ ሁለት ዓይነት አመለካከት እንዳለ ይታያል።

1. ቀዳሚው ቋንቋ ዕብራይስጥ ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። የእነዚህን ሰዎች ሐሳብ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ተደርጎ ከሚታየው ከመጽሐፈ ኩፋሌ[36] ላይ በሚከተለው መልኩ ማግኘት ይቻላል፤ ‹‹እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ አለኝ፣ ከውድቀት ቀን ጀምሮ ከሰው ልጅ ሁሉ ቋንቋ ተለይቶአልና የተገለጠች ቋንቋን ይሰማና ይናገር ዘንድ አፉንና ጆሮውን ክፈት። እኔም አፉንና ጆሮውን፣ ከንፈሩንም ከፈትሁ፤ <u>በትውልድ ቋንቋው</u>

[36] ይህን ሐሳብ በዚህ ክፍል ስር ማስቀመጥ የተፈለገው ‹‹መጽሐፈ ኩፋሌ›› የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ስለሆነ ሳይሆን እነርሱ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ነው ስለሚሉት ነው። መጽሐፉ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ከመሆን የሚጎድልበትን ምክንያት መረዳት የሚፈልግ አንባቢ ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› የሚለውን መጽሐፍ ይመልከት።



በዕብራይስጥ ቋንቋም ከእርሱ ጋር እናገር ጀመርሁ፤ የአባቶቹንም መጽሐፍ ወሰደ፤ እነዚያም በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ ነበሩ...›› (መጽሐፈ ኩፋሌ 11፡12-13)።[37]

2. **በአለቃ አያሌው ታምሩና በተከታዮቻቸው ዘንድ ግን ይህ ሐሳብ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም**

---

[37] በ1980 ዓመተ ምሕረት የታተመው ሰማንያ አሐዱ ይህን ሐሳብ በሚከተለው መልኩ ነው ያስቀመጠው፤ ‹‹ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔርም ምሥጢርን ግለጥለት፣ ዕዝነ ልቡናውም እንዲሰማ ይሁን፣ ጥቅመ ሰናዖር ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ የሰው ልጅ ሁሉ ከሚናገርበት ቋንቋ ተለይቶአልና የተረዳች ቋንቋን በአንደበቱ ይናገር ዘንድ ግለጥለት አለኝ። ምሥጢርን ገለጥሁለት፣ ዕዝነ ልቡናውም እንዲሰማ፣ አንደበቱም እንዲናገር አደረግሁ፤ ፍጥረቱ በተፈጠረበት በዕብራይስጥም ቋንቋ ከእርሱ ጋር እናገር ጀመርሁ፤ የአባቶችን መጽሐፍ ወሰደ፣ እነዚያም የዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈባቸው ናቸው››።

መጽሐፈ ኩፋሌ አንድምታም የሚከተለውን ያስነብባል፤ ‹‹ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር ምሥጢርን ግለጥለት አለኝ። ዕዝነ ልቡናውን እንዲሰማ አደረገው፣ በተረዳች ቋንቋ ባንደበቱ ይናገር ዘንድ ግለጥለት አለኝ። ጥቅመ ሰናዖርን፤ ነፋስ ገልብጦ ከጣለው ጀምሮ የሰው ልጅ ሁሉ ከሚናገርበት ቋንቋ ተለይቷልና። አፉን ጀሮውን አንደበቱን ገለጽኩት ማለት ምሥጢር ገለጽሁለት፤ ሲል ነው። በተፈጠረበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ከእርሱ ጋር እናገር ጀመርኹ፣ ቀድሞ በሰው ሁሉ አንደበት የምትነገር፣ ዛሬም በመላእክት አንደበት የምትነገር፣ ተዐርዓ፣ ተንጕሉ ሲል ነው፣ ከማየ አይኅ የጥቅመ ሰናዖር ጀምሮ የዕብራይስጥ ቋንቋ ከሰው ሁሉ አንደበት ጠፍቶ ነበርና፣ የአባቶቹን መጽሐፎች ወሰደ፣ እነዚህም የዕብራይስጥ ቋንቋ የጻፈባቸው ናቸው...›› (ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ኩፋሌ በአንድምታ ትርጓሜ (2005) ገጽ 131-132)።

በእነርሱ እምነት መሠረት ቀዳሚው ቋንቋ ዕብራይስጥ ሳይሆን ግእዝ ነውና። አለቃ አያሌው ‹‹ግእዝ ከእግዚአብሔር ተገኝቶ ተቀዳሚ ቋንቋ ለመሆኑ...›› ማስረጃ አለን ባሉበት መጽሐፋቸው ላይ ግእዝ ከልዑል እግዚአብሔር ተገኝቶ ለአዳምና ለልጆቹ የተሰጠና አዳምና እግዚአበሔር ይነጋገሩበት የነበረ ቋንቋ ነው የሚል ሐሳብ አቅርበዋል።[38]

በመጀመሪያ ስለተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ

የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ከሆኑት መጻሕፍት መካከል በመጀመሪያ የተጻፈው የትኛው ነው? የሚለውን በተመለከተ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንድ ወጥ የሆነ ትምህርት የለም። ለዚህም ራሱን ያረጋልን ጨምሮ የሚያቀርቡትን ልዩ ልዩ ሐሳብ እንደሚከተለው አስነብባለሁ ፤

1. ራሱ ያረጋል ቀድሞ ስለ ተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ስለሆነው መጽሐፍ ባሳፈረበት ላይ ‹‹ከሙሴ

[38] አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት (2003 - ሁለተኛ እትም) ገጽ 49-50።

በፊት መጽሐፍ አልነበረም›› ሲል ይህን ሐሳብ በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ‹‹እግዚአብሔር ለሰዎች ሕጉን በመጽሐፍ አስጽፎ የሰጣቸው ከአዳም በኋላ ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ቆይቶ ነበር›› በማለት አጽንቶታል።[39]

2. ከዚህ ሐሳብ ጋር የማይስማሙት ሰዎች ደግሞ ከሙሴ በፊት በሄኖክ እጅ በ1486 ዓመተ ዓለም የተጻፈ መጽሐፍ አለ የሚል እምነት ያላቸው መሆኑን አስፍረዋል (ኩፋሌ 5÷22-26)።[40]

---

[39] ያረጋል አበጋዝ (ዲያቆን)፣ መድሎተ ጽድቅ - ቅጽ 2 (ታኅሣሥ 2012) ገጽ 165፡ ገጽ 83 እና 85

[40] ዋኖስ አሳታሚ ድርጅት፣ መጽሐፍ ቅዱስ 66 ወይስ 81? (መጋቢት 1997) ገጽ 19። ዋኖስ አሳታሚ ድርጅት፣ መለከት መጽሔት (ታኅሣሥ 1985) ገጽ 4። አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ ኩሉሐ ሃይማኖት (የካቲት 1987) ገጽ 63። ዓባይነህ ካሴ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ (1992) ገጽ 49። ቸሬ አበበ (መምህር) እና ቴዎድሮስ በየነ (ዲያቆን)፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 1 (1996) ገጽ 45። ንጉሡ ዓለሙ (መምህር) የቱን እንቀበል? ክፍል አንድ (2005) ገጽ 29። መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርት ክፍል፣ ለቀዳማይ ተማሪዎች የተዘጋጀ መጽሐፍ (2006) ገጽ 136፡ 152፡ 175።

3. መጽሐፉ ኩፋሌ ደግሞ በሄኖክና በሙሴ መካከል በኖኅ እጅ የተጻፉ መጻሕፍት[41] መኖራቸውን ያሳያል (ኩፋሌ 10÷9)።

ስለዚህ ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› አላት የተባለችዋ ቤተ ክርስቲያን፣ አላት በተባለው መቆጣጠሪያና መለኪያ መሠረት፤ ቀድሞ የተጻፈው መጽሐፍ የቱ እንደሆነ ማሳወቅ ምነው ተሳናት? ያረጋልና ኩፋሌ፣ ኩፋሌና ሄኖክ፣ ሄኖክና አድማሱ ጀንበሬ፣ አድማሱ ጀንበሬና ዓባይነህ ካሴ… ‹እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው› አሉንሳ?

ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት ወይስ የለባትም?

በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ሐሳቦች ከሚቀርቡበትና የቤተ ክርስቲያን ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› የት ገባ? ከሚያሰኙት ነጥቦች አንዱ ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት/የለባትም የሚለው ርዕሰ ጉዳይ ነው። ከርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያለውን መከፋፈል ለማሳየት በነጥብ በነጥብ ማስቀመጡ የተሻለ

[41] መጽሐፉ ኖኅ ከአንድ በላይ መጽሐፍ ያዘጋጀ መሆኑን ይጠቁማል።

በመሆኑ ከዚህ በታች በሁለት በመክፈል ለማቅረብ ተሞክሯል፤[42]

1. ማርያም ጥንተ አብሶ የለባትም

- የቤተ ክርስቲያናችን ፓትሪያርክ አቡነ ማትያስ ወደ ፕትርክናው ከመምጣታቸው በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ተነሥቶ በነበረው ክርክር ወቅት፤ ‹‹አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ ኀጢአት (ጥንተ አብሶ) ያላገኛት ለመሆኗ በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠ ነው›› በማለት ማርያም ጥንተ አብሶ ያልነካት መሆኑን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡[43]

- ‹‹ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት›› የተሰኘው መጽሐፍ አዘጋጅ ድርሳነ ማርያምን ጠቅሰው ‹‹... ድንግል ማርያም ግን መንፈስ ቅዱስ ከእናቷ

[42] ይህን ርዕስ ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ ለመረዳት የአባ ሠረቀ ብርሃን ወልደ ሳሙኤልን ‹‹እውነትና ንጋት›› የተሰኘውን መጽሐፍ መመልከቱ ይጠቅማል፡፡

[43] ሠረቀ ብርሃን ወልደ ሳሙኤል (አባ/ቆሞስ)፣ (ታኅሣሥ 2004) እውነትና ንጋት ገጽ 43፡፡

ማኅፀን ጀምሮ ይህ ነው ተብሎ ሊነገር በማይችል ንጽሕናና ቅድስና አክበራት፣ ቀደሳት፣ አነጻትም...›› በሚል ያስቀመጡት ሐሳብ ማርያም ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ በቅድስናና በንጽሕና ተጠብቃ ነበረች የሚለውን ትምህርት መሠረት ያደረገ መሆኑ ግልጽ ነው።[44]

- የ‹‹ዓምደ ሃይማኖት›› መጽሐፍ አዘጋጅ ብርሃኑ ጎበናም ሉቃስ 1÷39-55 ያለውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ባስነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ‹‹...አንዳንዶች እመቤታችንን የአዳም ኀጢአት አለባት፣ ስለዚህ በደሙ ከተዋጁት ወገን ነች ይላሉ። ነገር ግን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአዳም ኀጢአት የሌለባት፣ በሥጋም በነፍስም ንጽሕት መሆንዋን መንፈስ ቅዱስ ከእናትዋ ማኅጸን ጀምሮ ያ በዘር የሚተላለፍ የመጀመሪያ ጥፋት ወደ እርስዋ እንዳይተላለፍ ጠብቋታል...›› በማለት

[44] አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር) ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (2000 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 129።

ማስረጃ ይሆነኛል የሚሏቸውን ጥቅሶች ለማስቀጥ ሞክረዋል።[45]

- ‹‹ገና በማኅፀን ከመፈጠሯ አስቀድሞ ከንጢአት፣ ከርኩሰት፣ ከጥንተ አብሶና ከምልአተ ኃጢአት ጠብቋታል። ከአባቷ ከኢያቄም አብራክ በዘርነት ወደ እናቷ ማኅፀን ስትላክ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ባወቀ ከንጢአት፣ ከበደል፣ ከርኩሰት፣ ከልማደ አንስት፣ ከአደፍና ከጉድፍ አጥልሏታል...›› የሚሉት ደግሞ ሊቀ ጉባኤ አባ ግርማ ናቸው። በእርሳቸው ሐሳብ መሠረት ከንጢአት የተጠበቀችው ‹‹... ገና በማኅፀን ከመፈጠሯ አስቀድሞ...›› ነው።[46]

እስከ አሁን እንደተመለከትነው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማርያም ከጥንተ አብሶ የጸዳች የነጻች ናት፤ የሚለውን ይመስላል። ያረጋል ቀደም ሲል በነገረን መሠረት ቤተ ክርስቲያን ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት››

[45] ብርሃኑ ኅበና፣ ዓምደ ሃይማኖት (1995 - ሰባተኛ ዕትም) ገጽ 101።

[46] የወልታ ጽድቅ ጸሐፊ የሊቀ ጉባኤ አባ ግርማ ርዕዩትን ‹‹ታኦዶክስ›› የተሰኘውን መጽሐፍ ጠቅሶ እንዳሰፈረው ገጽ 211-212።



አላትና ከዚህ ትምህርት የተለየ ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይኖርም ብሎ ማሰብ ተገቢ ይሆናል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ማንም እየተነሣ እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው የሚልባትና የግል አመለካከት የሚራመድባት ናትና ከዚህ የተለየ ትምህርት ያላቸው ሰዎች ሐሳብ ደግሞ ከዚህ በታች ይነበባል።

2. ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት

- መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ‹‹አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም፤ ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት። ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት፤ ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት፣ የመናገርና የገቢር ኀጢአት ፈጽሞ የለባትም››

በሚል የቤተ ክርስቲያን ነው የሚሉትን አቋም አንጸባርቀው ነበር።[47]

- በዚህ ርዕስ ስር ሌላው ተጠቃሽ ሰው ዓሥራት ገብረ ማርያም ናቸው። ትምህርተ መለኮት በሚል ርዕስ በወጣው መጽሐፋቸው በመጀመሪያው እትም[48] ላይ ‹‹በቤተ ክርስቲያናችን እምነት

[47] ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ እና ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (አባ)፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነትና የካህናት ተልእኮ (1982) ገጽ 29።

[48] ‹‹ትምህርተ መለኮት›› የተሰኘው መጽሐፍ ዳግመኛ ሲታተም ይህን ሐሳብ አንስተው (አስቀርተውት) ነበር። በ2006 ዓመተ ምሕረት መጨረሻ አካባቢ ጥቂት ጊዜ ከጋሽ ዓሥራት ጋር ለማሳለፍ ዕድሉን አግኝቼ ነበር። በነበረን ግሩም ውይይትም ላይም፣ ‹‹በመጀመሪያው ዕትም ላይ የነበረውን ማርያም የዘር ውርስ ኀጢአት ነበረባት የሚለው ሐሳብ በድጋሚ በታተመው መጽሐፍ ውስጥ እንዳይካተት የተደረገበት ምክንያት ምን ይሆን? እርስዎ የሐሳብ ለውጥ አድርገው ነው ወይስ ሌላ ምክንያት ተፈጥሮ?...›› የሚል ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፤ እሳቸውም፣ ‹‹እኔ ያደረኩት የሐሳብ ለውጥ የለም፤ የዚያን ጊዜ የነበረው እምነቱ አሁንም አለ፤ ሐሳቤን እንድለውጥ የሚያደርገኝ ነገርም የለም። እንዳልከው ግን ከመጽሐፉ ውስጥ ይህ ሐሳብ እንዲነሣ ተደርጓል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የመጽሐፉ መልእክት እርሱ ብቻ ባለመሆኑ ነው። አየህ! እኔ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማርያም የውርስ ኀጢአት አለባት የሚለውን ለማስተማር አይደለም የፈለኩት። እርሱ እግረ መንገድ የተሠራ ነገር ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከዚህ የተሻሉ ጠቃሚ ጠቃሚ ነገሮች አሉ። ነገር ግን ሰዎች ይህቺን አንድ ነገር መነሻ በማድረግ መጽሐፉ እንዳይነበብ ከፍተኛ ቅስቀሳ ጀመሩ። እንዳልኩህ የመጽሐፉ ዋነኛ መልእክት እሱ ባለመሆኑ እሱ ቢቀር መጽሐፉ የሚጎድለበት ነገር የለም በሚል እሱን በማውጣት መጽሐፉ ድጋሚ እንዲታተም ለማድረግ ተችሏል›› ነበር ያሉኝ።

መሠረት፡[49] ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1÷38 ላይ የመልአኩን ብሥራት ተቀብላ ‹እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ› ብላ እምነትዋን በእግዚአብሔር ላይ ባሳረፈች ጊዜ ጌታን ከመውለዷ በፊት መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ቀድሶና አንጽቶ የጥንቱን የአዳም ኀጢአት አስወግዶላታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞው የአዳም ኀጢአት የሚወረሰው በወንድ ዘር አማካይነት ልጅ በሚወለድበት ጊዜ ከአባት ወደ ልጅ በመሆኑና ጌታ ግን የተወለደው መንፈስ ቅዱስ የጥንቱን ኀጢአት ካስወገደላት ከእናት ብቻ ስለሆነ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት አልወረሰም…፡፡›› የሚለውን ሐሳብ አስፍረው ነበርና፡፡[50]

---

[49] ቀደም ሲል መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ‹‹… አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም፡፡…›› ማለታቸው ቀርቦ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ዐሥራት ገብረ ማርያም ‹‹… በቤተ ክርስቲያናችን እምነት መሠረት…›› በማለት ማርያም ጥንተ አብሶ ያለባት መሆኑን እያስነበቡ ነው፡፡ ይህ ማለት ማርያም ከዘር ውርስ ኀጢአት የነጻች የጸዳች ናት የሚለው ትምህርት ጊዜ ወለድ ሆኖ በተጽዕኖ ለማሸነፍ የቻለ ነው ማለት ነው፡፡

[50] ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ ትምህርተ መለኮት (1983) ገጽ 96፡፡

- አለቃ አያሌው ታምሩም[51] በሁለት መጻሕፍቶቻቸው ላይ ከዚህ በኋላ የሚነበቡትን ሐሳቦቻቸውን አቅርበዋል፤

  - መጽሐፍ አንድ፤ ‹‹...መርጦ ከኀጢአት አንጽቶ በመንፈስ ቅዱስ ቀድሶ ሥጋዋን ነፍስዋን ለተዋሐዳት ለእመቤታችን ድንግል ማርያምና ለተሰቀለበት መስቀሉ እንድንሰግድ ነው››።[52]

  - መጽሐፍ ሁለት፤ ‹‹ብዙ ዘመን ካለፈ በኋላ እግዚአብሔር ዓለምን በልጁ ሲዋጅና በክርስቶስ ሁሉ ዐዲስ እንዲሆን ሲፈቅድ መበሥር መልአክ ገብርኤል ወደ

[51] አለቃ አያሌው ታምሩ አቋም አልቦነት ይታይባቸዋል፤ ማርያም የውርስ ኀጢአት አለባት የሚለውን ሐሳብ በሁለት መጻሕፍቶቻቸው ያሰፈሩ ሲሆን፤ ‹‹ምልጃ እርቅና ሰላም›› በተሰኘውና ከሁለቱ መጻሕፍቶቻቸው በኋላ በታተመው መጽሐፋቸው ‹‹... ለእናትነት የመረጣትን ማደሪያውን ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ከኀጢአት፣ ከርኩሰት፣ ከእድፈት ሁሉ ጠብቋታል። የሰው ልጆች የተያዙበት፣ በአዳም በደል ወይም በራሳቸው በደል ምክንያት የረከሱበት የኀጢአት ቅሪት መርገም ሥጋ መርገመ ነፍስ የለባትም፣ አላገኛትም፤ ምክንያቱም እርሱ ለራሱ ማደሪያ አድርጎ ስለመረጣት ነው›› በማለት ሲያፈርሱት ይታያል (አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ ምልጃ ዕርቅና ሰላም። (1992)ገጽ 49)።

[52] አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት (2003 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 165።

እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መጥቶ ‹መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፤ የልዑል ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይበላል› አላት፡፡ በዚህ ቃል የድንግል ማርያም ሥጋዋም ነፍስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ ዐዲስ ሕይወት አገኘ፣ የልዑል ኃይል ወንድ ከማወቅ፣ ድንግልና ከማጣት፣ ዘር ከመቀበል በጠቅላላ ከዓለም ጠባይና ግብር ጠበቃት፤ ስለዚህ የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር እናት በመሆን ታደለች፤ በዚህ መሠረት ‹ሰውነቱ በአምላኬ በመድኀኒቱ ደስ ይላታል› ብላ ለመናገር በቃች፤ ሉቃስ 1÷35 እና 46››፡፡[53]

በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች መኖራቸውን፣ ማርያምን ከጥንተ አብሶ ጋር አያይዞ የሚቀርበው ይህ ሐሳብ ጥሩ ማሳያ ሆኗል ተብሎ ተስፋ

[53] አያሌው ታምሩ (አለቃ)፣ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ (ሐምሌ 1979) ገጽ 27-28፡፡

ይደረጋል። በዚህም ደግሞ ያረጋል ‹‹አለ›› ያለን ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› የት ነው ያለው? ብለን እንድንጠይቅ ምክንያት ይሆነናል።

የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ተብሎ የሚታመነውን ሁኔታ በተመለከተ

የቃል ኪዳኑን ታቦት በተመለከተ መጽሐፈ ዕዝራ ከዚህ የሚከተለውን ሐሳብ ያቀርባል፤ ‹‹የእግዚአብሔርንም ንዋየ ቅድሳት ትልቁንም ትንሹንም ሁሉ÷ የእግዚአብሔርንም ታቦት የንጉሡንም ቤት ዕቃ ሁሉ ዘርፈው ወደ ባቢሎን ወሰዱ›› በሚለው በዕዝራ ሱቱኤል ዘገባ መሠረት የቃል ኪዳኑ ታቦት በባቢሎናውያን ተዘርፎ ተወስዷል (ዕዝራ ካልዕ 1÷54 የ2000 ዕትም)።

ይህን የመጽሐፈ ዕዝራን ሐሳብ እርስ በእርሳቸው በሚጋጩ በሁለት መጻሕፍቶቿ ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችን አትቀበለውም።

1. ቤተ ክርስቲያን የቃል ኪዳኑ ታቦት አሁንም ድረስ በእጇ ላይ እንደ ሆነ ታምናለች፤ ያንንም ትናገራለች። እንደ ክብረ ነገሥት ዘገባ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በሰሎሞን የንግሥና ዘመን

ነው።።[54] እንደ ዕዝራ ካልዕ ደግሞ በሴዴቅያስ የንግሥና ዘመን ተዘርፎ ወደ ባቢሎን ተወስዷል። የሰሎሞንን የንግሥና መጨረሻ ዘመን 931 ቢወሰድና በሁለቱ ሰዎች መካከል የነበረውን ዘመን ልዩነት ለማወቅ ጥረት ሲደረግ የ344 ዘመን ልዩነት መኖሩን ማስተዋል ይቻላል። ማለትም በዕዝራ ካልዕ መሠረት የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ከተባለ ከ344 ዓመታት በኋላ ባቢሎናውያን ዘርፈው ወስደውታል። ስለዚህ ወይ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ያለው ክብረ ነገሥት፤ አልያም ደግሞ ባቢሎናውያን ወስደውታል የሚለው ዕዝራ ካልዕ ትክክል አይደለምና ከሁለቱ አንዱን ማረም አስፈላጊ ነው ማለት ነው። ይህም በያረጋል አለ የተባለው ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› የሌለ መሆኑን ያሳያል።

2. በተረፈ ኤርምያስ 8÷13 ላይ ‹‹ባሮክና ኤርምያስም ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ፤ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ስጧት፤ ምድርም

[54] ስርግው ገላው፣ ክብረ ነገሥት (መስከረም 1994) ገጽ 48።

ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠችው›› ከሚለው ሐሳብ ጋር አይስማማም፡፡ የተረፈ ኤርምያስ ጸሐፊ ‹‹የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ›› በምድር ከርስ እንደ ደበቁት ሲያስፍር የዕዝራ ካልዕ ጸሐፊ ደግሞ የለም ‹‹ንዋየ ቅድሳት ትልቁንም ትንሹንም ሁሉ›› ባቢሎናውያን ጠቅልለው ወስደውታል ይላል፡፡

በዚህም ደግሞ ‹አለ› የሚባለው ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› ከወሬ ያላለፈ መሆኑንና ሦስቱም መጻሕፍት ‹እኔ የተረዳሁት እንደዚህ ነው› ማለታቸውን እንመለከታለን፡፡ ስለዚህም ደግሞ አቶ ያረጋል እንዲሁ በከንቱ ‹አለ› በማለት ብቻ ሰውን ለማሞኘት ከሚሞክርና የሌላውን ‹ጉድፍ› ፈልጎ ለመተቸት ከመከጀሉ በፊት ዓይኑ ስር ያለውን ምሰሶ ይመለከት ዘንድ መጠቁሙ ተገቢ ነው፡፡

ሮሜ 8÷34 ላይ ያለውን ሐሳብ በተመለከተ

ከሮሜ 8÷34 ጋር በተያያዘ በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ዘንድ ጭንቀት መኖሩን በየጊዜው ከሚቀርቡት ጉራማይሌ ትምህርቶቻቸው መመልከት ይቻላል፡፡ ‹‹በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን

ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር አይችልም፤ መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት አላትና›› የሚለውን የያረጋል ባዶ ዲስኩር ውሃ እንዲበላው ከሚያደርጉት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ከዚህ ጥቅስ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡት ትምህርቶች ነው፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ነጥቦችን ይመለከቱና ‹‹በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር…›› እንደሚችል በራስዎ ያረጋገጡ፤

1. ‹‹የጠራው የግእዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ኀይለ ቃል ተለውጦና በዘመናት ሁሉ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን መቼም ቢሆን መልካም ዐስበው በማያውቁ ይልቁንም ፈራርሳ ቢያይዋት ደስ በሚሰኙ የክርስቶስን ፈራጅነት በካዱ በባሕር ማዶ ቀሣጪዎች ብዙ ጊዜ ተሰርዞ ተቀይሮ ይገኛል››፡፡[55]

በዚህ ጽሑፍ መሠረት ይማልዳል የሚለው መናፍቃን የጨመሩት እንጂ ትክክለኛ ትርጉም አይደለም፡፡ ነገር ጸሐፊው ማስተዋል የተሣነው ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን

[55] ሮዳስ ታደሰ (መጋቤ ዐዲስ)፣ ነገረ ክርስቶስ - ክፍል አንድ (የካቲት 2008) ገጽ 479፡፡



ጽሑፍ ለሮሜ ሰዎች የላከው ግእዝ የጽሑፍ ቋንቋ ባልነበረበት ዘመን መሆኑን ነው። ሐሳቡን ግልጽ ለማድረግ ይህ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ሲላክ ግእዝ ለጽሐፍ የማይመችና አናባቢ የሌለው ቋንቋ ነበር። በዚህም ምክንያት ግእዝ የሮሜን መልእክት ለማስተናገድ አቅም አልነበረውምና በግእዝ የተጻፈውን ምንጭ ማድረግ የተበከለ ምንጭ እንደ መጠጣት ይሆናል። ስለዚህ ማንም ብልህ አንባቢ ቀዳሚውን ምንጭ መፈለግ ግድ ይለዋል ማለት ነው።

2. ‹‹[መናፍቃን] ለማታለል ሲሉ በግእዝ ይማልዳል ብለው ጽፈውታል፤ ቃሉ ግእዝ ነው ግእዝና ፍቺውን የማያውቅ ሊታለል ይችላል። እነርሱ ግን ግእዝን ይቃወማሉ፤ ለማወናበጃ ግን ሊጠቀሙበት ይሞክራሉ። ቅዱስ ዳዊት ግን የቃልህ ፍቺ ያበራል... እንዳለ ፍቺው ይመሰክርባቸዋል። ምክንያቱም ይማልዳል የሚለው የግእዝ ቃል ሲሆን ፍቺው ይፈርዳል ነው። አማላጅ ቢሆን ኖሮ ቅዱስ ጳውሎስ በግልጽ ዐማርኛ ‹ያማልዳል› ብሎ በጻፈ ነበር።... እስኪ ፍረዱኝ››።[56]

[56] ደምሰው ዘውዴ (መምህር)፣ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ (2001) ገጽ 30።



ይሄኛው ደግሞ አስቂኝ የሆነ ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዐማርኛ የተጻፈ መስሎት ይሆን? ወይስ ምናልባት አብርሃም ኢትዮጵያዊ ነው፣ መልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ ነው፣ ማርያም ኢትዮጵያዊት ናት፣... እንደሚባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ኢትዮጵያዊ ነው እያለ ይሆን? እርሱ እንደ መሰለው መጽሐፍ ቅዱስ በዐማርኛ ቋንቋ የተጻፈ አይደለም። ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ዐዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆን መላው ዓለም (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ከእነዚህ ቋንቋዎች ነው ወደ የሀገራቸው ቋንቋ የተረጐሙት። የእኛ ሀገር ሰዎች (በተለይ ቤተ ክርስቲያናችን) ግን መጽሐፉን ወደ ዐማርኛ ሲተረጉሙት የግሪኩ የማይለውን በማስፈር እንግዳ ትምህርት ለማስተማር ምክንያት ሆኑ እንጂ።

ሌላው የዚህኛው ሰውዬ አስገራሚ ነገር ከላይ ከቀረበው ከጓደኛው ጋር አለመስማማቱ ነው። የላይኛው ጓደኛው የሚማልደው ሳይሆን የሚፈርደው ነው መሆን ያለበት የሚማልደው የሚለው የተቀየረ ነው ሲል ይህ ደግሞ የለም የሚማልደው ነው መሆን ያለበት ምክንያቱም የግእዝ ቃል ነውና። በግእዙ የሚማልደው ማለት የሚፈርደው ማለት ነው ይላል። ያረጋል ‹‹አለ›› የሚለው



‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› ዓይኑ እያየ አፈር እየበላው መሆኑን ለማየት አሁንም ማንበብዎን ይቀጥሉ፡፡

3. ‹‹ስለ እኛ የሚማለደው ተብሎ መጻፍ ሲገባው ‹ለ› ን ‹ል› በማድረግ ስለ እኛ የሚማልደው ተብሎ መጻፉና በዚህ መረዳቱ ፍጹም ስሕተት ነው፤ ከዚህም አልፎ ክሕደት ነው››፡፡[57]

ይሄኛው ደግሞ የፊደል ጨዋታ ውስጥ ገብቶ ይታያል፡፡ መምህሩ ‹‹ስለ›› የሚለው መስተዋድድ ‹‹የሚማለደው›› ከሚለው ጋር አብሮ እንደማይጫፈር አልገባው ይሆን? አሁንም ልብ አድርጉልኝ ይሄኛውም ከላይ ካሉት ከሁለቱ ጓደኞቹ ጋር አይስማማም፡፡ ከላይ ያሉት ሁለቱም ጥቅሱ ስለ ፍርድ እንጂ ስለ ምልጃ መጠቀስ የለበትም ባዮች ናቸውና፡፡ አረ እነዚህ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ተፋጨ እኮ!! ያረጋል ብቅ ብሎ ‹‹አለ›› በሚለው ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› መሠረት ለማስማማት ቢሞክር እንዴት መልካም ነበርiii

[57] በርሀ ተስፋ መስቀል (መምህር)፣ አንባቢው ያስተውል (መቐለ 2005) ገጽ 49፡፡

4. ‹‹ይህ ሕያው ሥጋውና ደሙ ሁል ጊዜ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርብ የሚኖር ከእግዚአብሔርም ጋር የመታረቂያው ብቸኛ መንገድ በመሆኑ አማለደን /አስታረቀን/ ሲል ገልጦታል››::[58]

ይሄኛው ደግሞ ከላይ ያሉት ሁሉም ትክክል አይደሉም:: ይልቁንስ አዎ ኢየሱስ አማላጅ ነው! ነገር ግን የሚያማልደው በቅዱስ ቁርባን ነው ይላል::

5. ቤተ ክርስቲያን ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› አላት የሚለው ያረጋልም ይህን ጥቅስ በተመለከተ ያቀረበው ሐሳብ አለ:: የእርሱም ሐሳብ ከላይ ከቀረቡት ጓደኞቹ የተለየ መሆኑን በራስዎ እንዲመለከቱ ከመጽሐፉ ላይ ቃል በቃል ከዚህ በታች ለማቅረብ እሞክራለሁ፤ ያረጋል ሮሜ 8÷34 ላይ ያለውን ምንባብ ካሰፈረ በኋላ፣ ‹‹ምን ማለት ነው?›› የሚል ጥያቄ ያቀርባል:: በመቀጠልም ራሱ ላነሣው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሲሞክር፤ ‹‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እስከሆነ ድረስ፣ አንድያ ልጁን ስለ እኛ አሳልፎ እስከ መስጠት ደርሶ

[58] ኃየሎም በርሄ (መሪጌታ)፣ ሁለቱ ኪዳናት (2002) ገጽ 219::



የወደደን እስከሆነ ድረስ፣ ዲያብሎስ ከሚያመጣው ፈተና እና በእግዚአብሔር ዘንድ ከሚያቀርበው ክስ የተነሣ አንፈራም ማለቱ ነውና ብፁዕና ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ ሰይጣን እኛን በእግዚአብሔር ፊት ሊከስ ቢሞክር፣ <u>ጌታችን የእኛ ዳኛ ብቻ ሳይሆን ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ የዋጀንና የገዛን ውድ ልጆቹና አካሎቹ ስለሆንን የሰይጣንን ክስ ውድቅ ያደርግበታል እንጂ አይቀበለውም ማለቱ ነው</u>፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ ዳኛ የእኛን ጉዳይ ለመፍረድ የሚቀመጥ ፈራጅ ብቻ ሳይሆን ልጆቹ፣ አካላቶቹ በመሆናችን የእኛ ክስ የእርሱም ክስ ነው፣ <u>ስለዚህ ዳኛችን ብቻ ሳይሆን እንደ ጠበቃ ስለ እኛ ክሳችንን ውድቅ ለማድረግ ማንኛውንም ነገር የሚጠቀም ነው</u>›› ይላል፡፡ ከዚህ አለፍ ብሎም ዮሐንስ አፈወርቅን ጠቅሶ የሚከተለውን ያስነብባል፤ ‹‹...ስለዚህ <u>ምልጃን የጠቀሰበት ምክንያት እርሱ ለእኛ ያለውን የፍቅሩን ጥልቀትና ብርታት፣ ፍቅሩ እስከ ምን ድረስ የሚዘልቅ ወሰን</u>



> <u>የለሽ መሆኑን ለመግለጽ እንጂ ሌላ ምክንያት እንዳልሆነ ተረዳ</u>...››።[59]

በዚህ በያረጋል ጽሑፍ መሠረት ቀደምት ነው የሚባለው ግእዙ ስሙ አልተነሣም፣ ፈራጅነቱን የሚያሳይ መሆኑም አልተወሳም፣ አማላጅ ነው ነገር ግን ምልጃው በቁርባን ነው የሚል የማለባበስ ሥራ አልተሠራም። ይልቁንስ እውነቱን ለመቀበልም ስሕተት የሆነውን ለመቃወምም የተቸገረ ሰው ይታያል። በዚህም ምክንያት ከላይ ካሉት ከአራቱም ጓደኞቹ ጋር የማይስማማ ሐሳብ ያስነብባል።

እነዚህ ሁሉም መምህራን ነን ብለው የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚቆሙ ቢሆንም በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ላይ እንኳ መስማማት ተስኗቸው ‹‹እኔ የተረዳሁት›› የሚል ትምህርት ማቅረባቸውን እያየን የአቶ ያረጋል ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› አለ የሚለውን ልግጫ ለመቀበል እንዴት ይቻላል?

---

[59] ያረጋል አበጋዝ (ዲያቆን)፣ መድሎተ ጽድቅ - ቅጽ 3 (ሚያዝያ 2012) ገጽ 224 እና 227 - አጽንዖት የግል።



የሰማንያ አሐዱ አቀባበልን በተመለከተ

የመጽሐፍ አካል የሆኑት መጻሕፍት የትኛዎቹ ናቸው? የሚለው ነጥብም እንዲሁ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች አንድ ዓይነት አቋምና አመለካከት እንደሌላቸው ያሳያል። በዚህም ‹‹በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንም ሰው ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር አይችልም፤ መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት አላትና›› የሚለውን የያረጋልን ሐሳብ ስንመለከተው ከንቱ ወሬ ብቻ መሆኑን ለማስተዋል ይረዳል።[60]

ቅዱስ ሲኖዶስ አዘጋጅቶት በ1975 ያሳተመው አነስተኛ መጽሐፍ ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 46 የብሉይ ኪዳን፣ 35 የዐዲስ ኪዳን፣ በድምሩ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት አሏት›› የሚለውን አስነብቦ ወደ ዝርዝሩ ሲገባ ግን መጽሐፈ ኩፋሌን፣ መጽሐፈ ሄኖክን፣ መጽሐፈ ዕዝራ ካልእንና ዕዝራ ሱቱኤልን እንዲሁም 3ኛ መጽሐፈ መቃብያንን <u>ከቍጥር ውጪ አድርጓቸዋል</u>። ከዚህም ሌላ ሁለቱ እንደ አንድ መቁጠር አለባቸው

[60] ከዚህ በታች የሰፈረው ሐሳብ ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ ነው።

የሚባሉትን 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤልን እንዲሁም 1ኛ እና 2ኛ ነገሥትን ለየብቻቸው ያስቀምጣቸዋል።[61]

‹‹ከቤተ ክርስቲያናችን ታላላቅ ሊቃውንት መካከል አንደኛው›› ናቸው የሚባልላቸው አለቃ አያሌው ታምሩ ከዚህ ሐሳብ ጋር ይስማማሉ፤ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን ጨምረው ከቁጥር ውጭ በማድረግ መጠነኛ ልዩነት አሳዩ እንጂ።[62] ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት›› የተሰኘውና ቤተ ክርስቲያን እምነቱ ይህ ነው ብላ ያሳተመችው መጽሐፍ 81 የመጻሕፍት ዝርዝርን ሲያስቀምጥ ጥበበ ባኅርንና መጽሐፈ ባሮክን ግን ረስቷቸዋል።[63]

---

[61] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር የታሪክ የሃይማኖት የሥርዓት መጽሐፍ (1975) ገጽ 68-71። ሣህሉ አድማሱ (መምህር)፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራል (የካቲት 2000 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 42-43።

[62] ሰይፍ የኅትመት እና የማስታወቂያ ሥራ ድርጅት፣ ሐዋርያ ኢትዮጵያ ጋዜጣ (ሰኔ - ሐምሌ 1991)፣ ገጽ 8።

[63] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት (ሐምሌ 1988) ገጽ 42-45። ቸርነት አበበ (መምህር) መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ (2005 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 43።

‹‹የቤተ ክርስቲያን ጸሎት›› የተሰኘው መጽሐፍ 80 የመጻሕፍት ዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ ዝርዝሩ ሲታይ ግን አንድ ላይ መቁጠር የነበረባቸው 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤልን፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥትን፣ ዕዝራንና ነህምያን ለየብቻ በመቁጠር፤ እንዲሁም በሌላ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ተረፈ ኤርምያስን፣ ተረፈ ዳንኤልንና መጽሐፈ ሶስናን በየራሳቸው አስቀምጦ ሲሆን፤ ከብሉይ ኪዳን 3ኛ መቃብያንን እና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን፣ ከዐዲስ ኪዳን ደግሞ ስምንቱን የሥርዓት መጻሕፍትን ከቁጠራ ውጪ አድርጓቸዋል፡፡[64]

‹‹ኩሩሐ ሃይማኖት›› የተሰኘው መጽሐፍ አዘጋጅ ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ፫፻ [318 ሊቃውንት] በአንቀጸ መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን ልትቀበላቸው የታዘዘ አምላክ ያጻፋቸው የአምላክን ነገር የሚናገሩ መጻሕፍት 81 ናቸው ብለው ዘርዝረው ደምረው በግልጽና በምሥጢር የቁጠሯቸውን መጻሕፍት እንዲህ ጠንቅቃ ቁጥራ ታምናለች›› በሚል 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ይዘረዝሩና ‹‹በአርባ ስድስቱ ላይ ሄኖክ፣ ኩፋሌ፣ ሱቱኤል

[64] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ የቤተ ክርስቲያን ጸሎት (1996) ገጽ 97-99፡፡

ዕዝራ ቢጨመሩ 49 ይሆናል። ስለ ሄኖክ የሰጠነው ሐተታ በቂ ነው። ኩፋሌ ዘተከፈለ እም ኦሪት ማለት ነው። ሱቱኤልም ያው ከላይ የተቈጠረው ዕዝራ ነው›› ይላሉ። በእሳቸው አቈጣጠር መሠረት ሄኖክ፣ ኩፋሌና ዕዝራ ሱቱኤል <u>ከቈጠራ መውጣታቸው ይታያል</u>። ከዚህም ሌላ ደግሞ በእሳቸው ቈጠራ መሠረት የመቃብያን መጻሕፍት ብዛት ሦስት ሳይሆን ሁለት ነው። ይህ ማለት እሳቸው ወደ ሰባት መጻሕፍት (በብሉይ ኪዳን ዐራት፤ ሄኖክን፣ ኩፋሌን፣ ዕዝራ ሱቱኤልንና ከመቃብያን መጻሕፍት ውስጥ አንዱን፤ ከዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሦስት፤ የዐዲስ ኪዳን ተጨማሪዎቹ መጻሕፍት ስምንት ቢሆኑም እሳቸው ግን አምስት አድርገው ነውና ያስቀመጡት) <u>አጉድለዋል</u>።[65]

‹‹መጽሐፈ ኢሚን ወሥርዓት›› በሚል ርዕስ መጽሐፍ ያዘጋጁት መምህር ዘበነ ለማ ‹‹ቤተ ክርስቲያናችን ትክክለኛ የሆኑትን መጻሕፍት ከብሉይና ከዐዲስ አንድ ሳይጓደል ይዛ የምትገኝ ከዓለም ብቸኛ ናት። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያት የተጠቀሙበትን ሙሉውን ሰማንያ አንድ (81) መጻሕፍት ስትጠቀም ካቶሊኮችና

[65] አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ ኰኵሐ ሃይማኖት (የካቲት 1989) ገጽ 92-94።

ፕሮቴስታንቶች ከዚያ ያነሰ እንደ የደረጃው ይቀበላሉ፡፡... እነዚህም ሰማንያ አንድ መጻሕፍት ሐዋርያት ቄጥረው ለቀሌምንጦስ[66] ከዚያም 318ቱ ቅዱሳን አበው እውነተኛውን ቄጥረው እነሱም ተቀብለው ለክርስቲያኖች መመሪያ ይሆን ዘንድ የእነዚህም የብሉይና የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስምና ቍጥር ከዚህ እንደሚከተለው ነው›› በማለት ዝርዝሩን ሲያሰፍሩ አንድ ላይ መቁጠር የሚገባውን ዕዝራ ሱቱኤልና ዕዝራ ካልዕን ‹‹መጽሐፈ ዕዝራ ቀዳማዊ እና መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ›› በማለት ለየብቻ ይቈጥሯቸዋል፡፡ እንዲሁም ደግሞ አንድ ላይ መቁጠር የሚገባውን ሁለተኛ እና ሦስተኛ መቃብያንን ለየብቻ በማስቀመጥ 46 የብሉይ ኪዳን የመጻሕፍት ዝርዝር ያቀረቡት በአንድ ላይ መቁጠር የሚገባቸውን

[66] በጸሐፊው እምነት መሠረት ሐዋርያት ለቀለሜንጦስ ሰማንያ አንድ መጻሕፍት ቄጥረው ለመስጠት በእነርሱ ጊዜ ሰማንያ አንዱም መጻሕፍት ተጽፈው አልቀው ነበር ማለት ነው፡፡ መጻሕፍቱ የተጻፉበትን ዘመን መመርመሩ ግን እውነቱ ከዚህ የራቀ መሆኑን ያሳያል፡፡ መጻሕፍቱ መቼ ተጻፉ? በዚያስ ዘመን ሁሉም ሐዋርያት በሕይወት ነበሩ ወይ? የሚለውን በመጠኑ ለማየት ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ ስለዲድስቅልያ በተጻፈበት ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት ‹‹መጽሐፉን የጻፈው ማን ነው?›› በሚለው ርዕስ ስር የቀረበውን ጽሑፍ ይመልከቱ፡፡

ነህምያንና ዕዝራን እንዲሁም መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን በማጉደል ነው።[67]

‹‹የቱን እንቀበል?›› የሚለው መጽሐፍ አዘጋጅ በበኩላቸው ‹‹ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር 81 ሲሆን እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት ጠብቃ ለትውልድ በማስተላለፍ አደራዋን የተወጣችና በመወጣት ላይ የምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን በሙሉ ልብ መናገር እንችላለን›› ብለው መጻሕፍቱን ሲዘረዝሩ፤ መጽሐፈ ኩፋሌን፣ መጽሐፈ ሄኖክን፣ ዕዝራ ካልእና ዕዝራ ሱቱኤል፤ 3ኛ መቃብያንን እና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን ትተዋቸዋል።[68]

አቶ ዓሥራት ገብረ ማርያም ‹‹ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት›› በሚለው ርዕሳቸው ስር ‹‹መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ ጥበበ ሰሎሞን፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ አንደኛ እና ሁለተኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ባሮክ እንዲሁም ተረፈ ዳንኤልና ተረፈ

[67] ዘበነ ለማ (መምህር)፣ መጽሐፈ አሚን ወሥርዓት (ሚያዝያ 2009) ገጽ 104-109።

[68] ንጉሡ ዓለሙ (መምህር)፣ የቱን እንቀበል? ክፍል አንድ (2005) ገጽ ii እና 37።

አስቴር››ን ሲያስቀምጡ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣ ዕዝራ ካልእና ዕዝራ ሱቱኤል፣ ሦስተኛ መቃብያንና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን አላካተታቸውም።[69]

‹‹... የብሉያትንና የዐዲሳትን መጻሕፍት ቍጥር ምንም ሳይቀንስና ሳይጨምር የሰማንያ አንዱን መጻሕፍት ቍጥር ዘርዝሮ ጽፏል››[70] ተብሎ የተመሰከረለት ‹‹መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት›› የተሰኘው መጽሐፍ ደግሞ፤ መጽሐፈ ነህምያና መጽሐፈ ዕዝራን (ሁለቱ መጻሕፍት እንደ አንድ ነው የሚቈጠሩት) እና ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን ያጎድላል።[71]

የቤተ ክርስቲያን ልሳን የነበረውና በ1982 ዓመተ ምሕረት የታተመው ‹‹ትንሣኤ›› መጽሔት ‹‹ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሄኖክንና ኩፋሌን ትቀበላቸዋለች›› ይልና ‹‹ግን እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ከ81 ጋር

---

[69] ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ ትምህርተ መለኮት (2005) ገጽ 128። ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ ፍኖተ ብርሃን (1993) ገጽ 147-153።

[70] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ፤ ከውሸትና ከክፉ አድራጊዎች ተጠበቁ (ጥር 2009) ገጽ 40።

[71] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት (1988) ገጽ 145-147።

አይቁጠሩም›› በሚል ከቍጥር ያወጣቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ 3ኛ መቃብያንን ሳይጠራው አልፏል፡፡[72]

ዐሥራት ከበደ የተረጎመው ‹‹መጽሐፈ ጦቢት›› የተሰኘው መጽሐፍ መጽሐፈ አስቴርን የተጨማሪዎቹ መጻሕፍት አካል አድርጎ ሲስቀምጥ 3ኛ መቃብያንን፣ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን፣ ሄኖክንና ኩፋሌን አይቁጥራቸውም፡፡[73]

‹‹እንድትጸኑባቸው ያዘዝናችሁ መጻሕፍት እነዚህ ናቸው፡፡ ከሐድያን ከአስቀመጧቸው የሐሰት መጻሕፍት የወሰደና ንጽሕት የሆነች የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደ ሆነች አድርጎ ሕዝብን ለማሳሳት ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ያገባ ሰው ቢኖር ይለይ›› የሚለው ‹‹ፍትሐ ነገሥት›› ደግሞ እንደ ‹‹መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት›› ሁሉ መጽሐፈ ነህምያንና መጽሐፈ ዕዝራን ትቷቸዋል፡፡ በአንጻሩ እንደ አንድ መቁጠር ይገባቸዋል የሚባሉትን ሁለቱን በአንድ ይቁጥራቸውና ሲደምር ግን፣ ሁለቱን መጽሐፈ ሳሙኤል፣ ሁለቱን መጽሐፈ ነገሥት፤ እንዲሁም መጽሐፈ ዕዝራ ካልእና ዕዝራ ሱቱኤልን

[72] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስበከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ትንሣኤ መጽሔት (መጋቢት ሚያዝያ 1982) ገጽ 1 እና 11፡፡
[73] ዐሥራት ከበደ (ትርጉም)፣ መጽሐፈ ጦቢት (2005) ገጽ 13-14፡

በተናጠል ይደምራቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ፍትሐ ነገሥት መጽሐፈ ኩፋሌን ‹‹ነውር ስለ ተገኘበት›› ብሎ ከቀኖና ሲያስወጣው፤ ሄኖክንም እንዲሁ ሊቈጠር እንደማይገባው በግልጽ ይናገራል፡፡[74] ለዚህ ሳይሆን አይቀርም አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሄኖክንና ኩፋሌን ‹‹አዋልድ››[75] በማለት የጠሯቸው፡፡[76]

በዚህ ዓይነት የሂሳብ ስሌት ነው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና ዝርዝር ወደ 46 ለማድረስ ጥረት እየተደረገ

---

[74] መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት (1994)፣ ገጽ 57፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ፍትሐ ነገሥት (1995 - ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ) ገጽ 43፡፡ አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ፍትሐ ነገሥት (1962) ገጽ 23፡፡ አሳታሚው ያልተገለጸ፣ ፍትሐ ነገሥት (ሚያዝያ 27/1958) ገጽ 43፡፡

[75] ‹‹ለሃይማኖት ምስክር የማይሆኑ ከመጻሕፍተ ብሉያትና ከዐዲሳት እየተቀዱ እየተዉጣጡ የተጻፉ ገድልና ድርሳን፣ ሌሎችም ልዩ ልዩ አዋልድ መጻሕፍት አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ›› (ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (2005 - ሦስተኛ ዕትም) ገጽ 788)፡፡ ‹‹ ‹አዋልድ - ልጆች› ከሙሉ እድገት ያልደረሱ ማለት ነው፡፡ መጻሕፍቱንም አዋልድ ሲሏቸው ‹የልጅ ነገር እንዲሉ› ስለ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ምስክር የመሆን ብቃት እንደሌላቸው ለማስረዳት ነው›› (ማኅበረ በኩር፣ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 20፤ ገጽ 5)፡፡

[76] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ (1948) ገጽ 19፡፡

ያለው።[77] በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያገኙት መጻሕፍት የትኛዎቹ ናቸው? የሚለውን ለማወቅ ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ ይረዳል ተብሎ ይታሰባል፤

[77] መሪራስ አማን በላይ ከዚህ በላይ ከሰፈሩት ጋር ጨርሶ የማይገጥም አቁጣጠር ያስነብባሉ። የእርሳቸውን አቁጣጠርና የመጽሐፍ ዝርዝር ከላይ ከሰፈሩት ጋር በምንም የማይገጥም በመሆኑ አብሮ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ነገር ግን ለአንባቢ ይረዳ እንደ ሆነ በግርጌ ማስታወሻ እንደሚከተለው ተቀምጧል። እርሳቸው በስም ዘርዝረው ያስቀመጧቸው መጻሕፍት ብዛት 101 ነው። ይህን ያህል ልዩነት የፈጠሩት ባሉት ላይ በመጨመር ብቻም ሳይሆን እነ ኩፋሌንና ሄኖክን በማጉደልም በመሆኑ እነዚህ መጻሕፍት ቢጨምሩ ቁጥሩ ወደ 103 ከፍ ባለ ነበር። ወደ 101 ያሳደጉትም እስከ አሁን ድረስ ተሰምተው የማይታወቁ መጻሕፍት በመጨመር ነው፤ እነርሱም፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትንቢተ ኢሳይያስን ጽፈው ሲያበቁ እንደገና ደግሞ መጽሐፈ ኢሳይያስ የሚል አክለው፣ ከመዝሙረ ዳዊት ጋር መጻሕፍተ ኤልያስ ወሰረገላ ኤልያስ የሚል መጽሐፍ አስቀምጠው፣ መጽሐፈ ሲራክ እያለ ሌላ ደግሞ መጽሐፈ ምክረ ሰናይ ዘአክሱማዊ ሲራክ የሚል ደምረው፣ መጽሐፈ አስቴርን ቀዳማዊና ካልዕ በማለት ሁለት አስቴር አስቀምጠው፣ ትንቢተ ኤርምያስ እና ሰቆቃወ ኤርምያስ እያለ መጽሐፈ ኤርምያስ የሚል ጨምረው (ተፈረ ኤርምያስ ማለታቸው ይሆን?) ዜና አይሁድ (ምናልባት ዜና አይሁድ ብለው ያሰፈሩት ፍትሐ ነገሥት መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ያለውን ይሆን?) ቀዳማዊና ካልዕ ብለው በማስፈር ሲሆን በዐዲስ ኪዳን ደግሞ የያዕቆብ መልእክትን ‹‹የያዕቆብ መልእክቶች›› በማለት ከአንድ በላይ በማድረግ (መልእክቶች የሚል አሰፈሩ እንጂ ስንት እንደ ሆኑ አላሳዩምና ከሁለትም በላይ ሊሆን ይችላል) ትርጓሜ ዘዮሐንስ ራእይ (ይህ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ያለ ቢሆንም ከሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት ውስጥ ገብቶ የሚቁጠር ሳይሆን የዮሐንስ ራእይ ማብራሪያ ሆኖ ነው የሚታየው) የማቴዎስ ወንጌልን አስፍረው ሳለ የማቴዎስ መልእክት የሚል በመጨመር፣ አክሲማሮስን፣ መጽሐፈ ሐዊን፣ መጽሐፈ አቡሻክርን፣ መጽሐፈ ሳዊሮስን፣ መጽሐፈ ነገረ ማርያም ወዜና ማርያምንና መጽሐፈ ራእየ ማርያም ሁለት ዓይነት (እነዚህ

የተጨማሪ ምቹ መጻሕፍት ዝርዝር	የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. አጭር የሃይማኖት የሥርዓት መጽሐፍ	ትንሣኤ መጽሔት	የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት	መልአክ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ	መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት	አለቃ አያሌው ታምሩ	ዓሥራት ገብረ ማርያም	ፍትሐ ነገሥት	የቤተ ክርስቲያን ጸሎት	ዐሥራት ከበደ
መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል	×	✓	✓	×	✓	×	×	✓	✓	✓
መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ	×	✓	✓	✓	✓	×	×	✓	✓	✓
መጽሐፈ ጦቢት	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓

መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ያሉና አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ቢሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ተደርገው የሚቆጠሩ ግን አይደሉም) በመጨመር ነው። ጸሐፊው እነዚህን መጻሕፍት የብሉይና የዐዲስ ኪዳን አካል አድርገው ሲያስቀምጡ የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ተከትለው እንደ ሆነ ያሰፈሩት ነገር ግን የለም (አማን በላይ (መሪ ራስ) የልቤ ወዳጅ፣ የሰው ዘር ልጅ (2008) ገጽ 174-179)።



መጽሐፈ ዮዲት	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
1ኛ መቃብያን	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
2ኛ መቃብያን	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
3ኛ መቃብያን	×	×	✓	×	✓	×	×	✓	×	×
መጽሐፈ ሲራክ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
ጸሎተ ምናሴ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
ተረፈ ኤርምያስ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ሶስና	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ባሮክ	✓	✓	×	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ጥበብ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
ተረፈ ዳንኤል	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ኩፋሌ	×	×	✓	×	✓	×	×	×	×	×
መጽሐፈ ሄኖክ	×	×	✓	×	✓	×	×	×	×	×
መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን	✓	✓	✓	✓	×	×	×	×	✓	×



ሁሉም የተቀበሏቸው መጻሕፍት፤ መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ 1ኛ መቃብያን፣ 2ኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ ጸሎተ ምናሴ፣ ተረፈ ኤርምያስ፣ መጽሐፈ ሶስና፣ መጽሐፈ ጥበብ፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅና ተረፈ ዳንኤል ናቸው። ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ጸሎተ ምናሴ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ፣ ተረፈ ኤርምያስ ትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ፣ መጽሐፈ ሶስና፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅና ተረፈ ዳንኤል ትንቢተ ዳንኤል ውስጥ እየገቡ የሚቈጠሩ በመሆናቸው ከ66ቱ መጻሕፍት ጋር አብረው ሊቈጠሩ የሚችሉት መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ 1ኛ መቃብያን 2ኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ሲራክ እና መጽሐፈ ጥበብ ብቻ ናቸው ማለት ነው።

በጥቅሉ ግን የመጻሕፍቱን ብዛት 81 ለማድረግ ገና ችግር እንዳለ ይታያል።[78] ይህን ያስተዋሉት መምህር ቸርነት አበበ ‹‹በተለያዩ ጊዜያት ማለትም በ1918፣ 1929፣ 1947 (1953) እና 1980 ዓመተ ምሕረት[79] የታተሙት መጽሐፍ ቅዱሶች ዝርዝር አንዱም ግልጽ በሆነና ቁርጥ

[78] ማኅበረ በኩር፣ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 20፣ ገጽ 5-10።
[79] በ2000 ስለታተመው ሰማንያ አሐዱ አስተያየት ያልሰጡት ምናልባት ‹‹ግልጽ በሆነና ቁርጥ ባለ ሁኔታ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞች እንደ ሆኑ›› አመላክቷል ብለው ይሆን?



ባለ ሁኔታ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ አያሳይም›› ብለዋል።[80]

ያረጋል መለኪያ አድርጎ ያስቀመጠው መርሐ ትምህርት ምን ዋጠው? ሰማንያ አሐዱን በተመለከተ አባቶችና የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እንዲህ እየተናጨና እየተንጫጩ ምነው ዝም ማሰኘት አቃተው?

[80] ቸርነት አበበ (መምህር)፣ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ (2005 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 43።



ማጠቃለያ

አንዳንዶች በንግግር ችሎታቸው ሌሎች ደግሞ ባላቸው ተቀባይነት ሐሰቱን እውነት በማስመሰል በሕዝቡ ልብ ውስጥ የተሳሳተ ትምህርታቸውን ለመዝራት የተቻላቸውን ያህል ይደክማሉ፡፡ በዚህ ጎዳና ላይ እየሄዱ ካሉት ሰዎች መካከል አንዱ የመድሎተ ጽድቅ መጽሐፍ አዘጋጅ ነው፡፡

ራሱን መዛኝ ሌሎች ደግሞ በእርሱ ሚዛን ላይ ተቀምጠው እንዲህና እንዲያ የሚባሉ አድርጎ የሳለው ያረጋል ‹‹አለኝ›› የሚለው እውነትና ‹‹ትክክል›› ነው የሚለው ትምህርት ሚዛን ላይ ሲቀመጥ ከእውነታ የራቀ መሆኑ ይታያል፡፡

ለዚህም ቀደም ሲል የቀረቡት ሐሳቦች ጥሩ ማሳያ ይሆናሉ፡፡ እንደ ያረጋል ሐሳብ ቤተ ክርስቲያን ‹‹መቆጣጠሪያና መለኪያ መርሐ እምነት›› ባለቤት በመሆኗ በየትኛውም ጉዳይ ላይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ወጥ የሆነ ትምህርት አላቸው ተብሎ መጠበቁ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ያረጋል ‹‹...በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንም ሰው



ተነሥቶ የራሱን ግምትና ስሜት በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ማስተማር አይችልም...›› ብሎናልና፡፡

ነገር ግን ቀደም ሲል በቀረቡት ናሙናዎች ለመታዘብ እንደቻልነው በአንድ ሐሳብ ላይ መስማማቱ ቀርቶ የማይገናኙ ሁለትና ከዚያም በላይ ሐሳቦች ይቀርባሉ፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም አንድ ሰው አንድ ጊዜ ያስተማረውን ትምህርት መልሶ ሲያፈርስና ዐዲስ ትምህርት ሲያቀርብም አይተናል፡፡

በያረጋል ‹‹አለ›› የተባለው መርሐ እምነት ከንግግር ያልዘለለና በተግባር ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም፡፡ የሌለውን ነገር አለ ለማለት የተፈለገበት ምክንያት ሌሎችን ለመተቸት እንዲረዳ ብቻ ነው፡፡

ምንም እንኳ በውሸት የሚደምቅ እውነት ባኖርም ሰዎቻችን አለን የሚሉትን ‹‹እውነት›› ከፍ አድርገው ለማሳየት ውሸትን መሠረት ማድረግ መጀመራቸውን ይህ የያረጋል ሥራ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ እባክህ ከአንተ በሆነው እውነት ጸንተን የአንተን እውነት ብቻ ለመመስከር እርዳን!!!



የአዘጋጁ ልሎች ሥራዎች

ታትመው ለንባብ የበቁ

- የብልጠት ተረቶች፣
- አታስቀኑት፣
- ኢየሱስ እውነተኛ አማላጅ ጻድቅ ፈራጅ፣
- ለተኣምረ ማርያም አትክራከር (አሁን በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
- የዲያብሎስ ማስታወሻ ደብተር (አሁን በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
- ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን።

በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) ለንባብ የበቁ

- ሃይማኖታዊ እንክርዳድ ቅጽ - ፩፣
- በውኑ ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ አላትን?
- ነህምያ ከደረሰበት ተቃውሞና ለተቃውሞው ከሰጠው ምላሽ ምን እንማራለን?
- የማን ባሪያ ነዎት?
- ሰማንያ አሐዱ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም!!!

በዝግጅት ላይ ያለ

- ሃይማኖታዊ እንክርዳድ ቅጽ - ፪
- ሮሜ 8÷34 እና የ1938 ዕትም ዐዲስ ኪዳን